# የትውን እና የእይታ ጥበባት

## የመምህሩ መምሪያ




2ኛ ክፍል

# የትውን እና የእይታ ጥበባት

## የመምህሩ መምሪያ

## 2$^{ኛ}$ ክፍል

**አዘጋጆች፡-** አምዶም ገ/ዮሃንስ

ርብቃ ፀጋየ

ጉማይዴ ጉልአ

**አርታኢ፡-**

ምንያህል በቀለ

**ሰዓሊ፡-** አምዶም ገ/ዮሃንስ

**ኖታ ቀራጭ፡-** ርብቃ ፀጋየ

**የጥራት ተቆጣጣሪ(ፓናሊስት)፡-** ተክለማርያም ጥላሁን

- ተዋበ ታደሰ

**አጽዳቂዎች(ቫሊዴተር)፡-**ተስፈዬ እሸቱ

ሲዳሞ ሳለሰ

ቅድስት የሱፍ

ዋንቱሳ ጉንሳ

ይመኙሻል ዩሱፍ

ሀብታሙ ጳውሎስ

## መግቢያ

ይህ መፅሐፍ  የትውን እና የእይታ ጥበባት ለሁለተኛ ክፍል ሲሆን በአከባቢያችን ከሚገኙ ተፈጥሮኣዊ እና ሰዉ ሰራሽ ቁሶች  የሚቆራኙ እሴቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ትውኔት ፤የእይታ ጥበብ እና የሙዚቃ ኖታዎችን በመጠቀም መስመሮች እና የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን በመጠቀም የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች የትውን እና የእይታ ጥበባትን ተጠቅመው በእየለቱ የሚያስተውሏቸውን ነገሮች መነሻ በማድረግ የትውን እና የእይታ ጥበባትን መለየትና የፈጠራ ያላቸውን ልምድ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## የሚጠበቁ ውጤቶች

**ከዚህ የክፍል ደረጃ በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ያውቃሉ
- ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ይለያሉ
- ፎቶዎች እና ምስሎችን ለይተው ያውቃሉ
- መስመሮች በመጠቀም ንድፎችን ይለማመዳሉ
- ሙዚቃ፣ውዝዋዜ እና ተውኔት በመጠቀም ተዛማጅ ታሪኮችን ይከውናሉ
- በከባቢያቸው ላይ ያሉ ቀለማትን ይለያሉ
- እና የእይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች  ያለው ግንኙነት ይገልፃሉ

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

**ምዕራፍ 1፡ መለየት ........................................ 1**

1.1. የሙዚቃ ኖታዎችን እና እረፍቶችን መለየት ........................................ 2

1.2 ቀለል እንቅስቃሴዎች እና ውዝዋዜዎችን መለየት ........................................ 6

1.3 ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ማየት ........................................ 8

1.4. ፎቶግራፎችን መመልከት ........................................ 10

1.5. የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን መለየት ........................................ 23

**ምዕራፍ 2፡ ፈጠራዊ አገላለፅ ........................................ 28**

2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መጫዋት ........................................ 28

2.2 ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ........................................ 32

2.3 ቀላል የትወና ጨዋታዎችን መጫወት ........................................ 33

2.4. ቀላል መስመሮች በመጠቀም ንድፎችን መለማመድ ........................................ 34

**ምዕራፍ 3፡ ሀገረ-ሰባዊ ምልከታዎች ........................................ 43**

3.1 ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ........................................ 44

3.2 ተዛማጅ ታሪኮች ........................................ 52

3.3 ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቀለማት እና ትወና ከባህላዊ ምልከታዎች አኳያ ........................................ 54

3.3.1. ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ........................................ 55

3.3.2. ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ........................................ 55

3.3.3. ትወና ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ........................................ 64

**ምዕራፍ 4፡ አድናቂነት ........................................ 66**

4.1 የትውን እና የእይታ ጥበብ ክንዋኔዎች ........................................ 66

**ምዕራፍ 5፡ ግንኙነት ........................................ 79**

5.1 በሰውነት አካላት የሚሰሩ ሙዚቃዎች ........................................ 80

5.2. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነት ........................................ 84

5.3 የትወና እና የእይታ ጥበባት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለማገዝ ያለው ሚና ... 87

5.3.2 ሙዚቃ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያለው ጠቀሜታ ........................................ 90

5.3.3 ስነ-ጥበብ የጤና እና ሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ .. 94

5.3.4 ስነ-ጥበብ የሂሳብ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ ........................................ 95

5.3.5 ስነ-ጥበብ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸው ........................................ 95

5.3.6 ስነ-ጥበብ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን ለመማር ያለው ጠቀሜታ ........................................ 99

| | |
|---|---|
| **ምዕራፍ**<br><br>**1** | **መለየት** |

| | |
|---|---|
| ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 25 |

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ከመዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- የሙዚቃ ኖታዎችን እና ቀላል እንቅስቃሴ ይለያሉ
- ልጆች ግማሽ ድምፅ ተጠቅሞየሚዘመሩ ሙዚቃዎችን ይለያሉ፡፡
- ፎቶ ወይም ምስል በመመልከት ሀሳቡን ይረዳሉ፡፡
- ፎቶ ወይም ምስል በመመልከት አከባቢያቸው እና ሃገራቸውን ያውቃሉ፡፡

## 1.1. የሙዚቃ ኖታዎችን እና እረፍቶችን መለየት

| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 5 |
| --- | --- |

**መግቢያ**

በሙዚቃ ውስጥ ያሉ የሙዚቃ ኖታዎች የዕረፍት ምልክቶች በርካታ ናቸው፡፡ ለዚህ ክፍል ደረጃ በዚህም ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና የሙዚቃ ኖታዎች (የዕረፍት) ምልክቶች ይለያሉ፡፡
እነዚህም ሙሉ ኖታ (ሙሉ ዕረፍት) እና ግማሽ ኖታ (ግማሽ ዕረፍት) ይሆናል፡፡

### ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን እና የዕረፍት ኖታዎችን ከሙሉ እስከ ግማሽ ይለያሉ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን ሙሉና ግማሽ እንዲሁም የጊዜ ዋጋን ያውቃሉ፡፡
- ሙሉ እና ግማሽ ኖታዎችን እና የዕረፍት ኖታዎችን ቅርፅ ይለያሉ፡፡
- የተለያዩ ሙዚቃዊ እንቅስቃሴዎችን እና ውዝዋዜን ይሰራሉ፡፡

### ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

እርሳስ

ላጲስ (ማጥፊያ)


ወረቀት

## ጠቃሚ መረጃ


ሙሉ ኖታ በውስጡ 4 ምት እንዳለው እና በጊዜ ዋጋ ከሁለት ግማሽ ኖታ ጋር እኩል እንደ ሆነ ማስረዳት፡፡ እና ለተማሪዎች ይህንን ኖታ በመጀመሪያ እንዲመለከቱ ማድረግ እና ለመሳል እንዲሞክሩ ማለማመድ፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

- ስለ ሙዚቃ እና ስለ ሙዚቃ ኖታዎች ከዚህ በፊት ምን ያህል እውቀት እንዳላቸው በቃል ጥያቄ መጠየቅ
- የሙዚቃ ኖታ ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ማድረግ
- ስለ ኖታ እና የእረፍት ምልክት ልዩነት ተማሪዎች ለይተው ማወቃቸውን መገምገም



ይህን አራት የቆይታ ጊዜ ያለውን ኖታ ሁለት ቦታ በመክፈል ከሁለት ግማሽኖታ ጋራ እኩል እንደ ሆነ አሳዩ፡፡




እነዚህን ግማሽ ኖታዎች በመደመር ከአንድ ሙሉ ኖታ ጋር እኩል እንደሆነ ይንገሩዋቸው፡፡

## ሙሉ የዕረፍት ምልክት


ሙሉ የዕረፍት ምልክትም በጊዜ ዋጋው ከሙሉ ኖታ ጋር እኩል ሲሆን ይህን ምልክት በሙዚቃ ስናስገባው በዝምታ (ድምፅ አልባ) ሆኖ አንገታችንን በመወዝወዝ ወይም በውስጣችን ድምፅ ስነወጣ አራት መቁጠር እንደሆነ ለተማሪዎቹ በተግባር ያሳዩዋቸው፡፡




ግማሽ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ ሁለት ምት (ስልተምት) አለው፡፡ ተማሪዎች ይህንን ግማሽ ኖታ በመደመር ዘዴ እንዲለማመዱ ያሳይዋቸው፡፡
መምህር ይህን እንዲዘምሩ ያበረታትዋቸው



ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ



ሁለትየዝምታ ጊዜ

## ግማሽ የእረፍት ምልክት

ግማሽ የዕረፍት ምልክትም በጊዜ ዋጋ ከሁለት ሩብ የዕረፈት ምልክት ወይም ከአራት ንዑስ የዕረፍት ምልክት ጋር እኩል እንደሆነ ያሳዩ፡፡ ይህ ምልክት ሲያነቡ ድምፅ አልባ እንደሆነ እና በተለያዩ ምልክት ሁለት የቆይታ ጊዜ እንዳለ መምህር/ት/ያሳይዋቸው፡፡



እነዚህ የሙዚቃ ኖታዎችና የጊዜ ቆይታቸው

| የሙዚቃ ኖታዎች ስም | ያላቸው የጊዜ ቆይታ | የዕርፍት ምልክት |
|---|---|---|
| O ሙሉ ኖታ | 4 ምት በድምፅ | በዝምታ  |
| 𝅗𝅥 ግማሽ ኖታ | 2 ምት በድምፅ | በዝምታ  |

ሰንጠረዥ 1.1፡ የሙዚቃ ኖታዎች ስም እና ምልክቶች

**መልመጃ 1.1**

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱን ያስቀምጡ

1) በሙዚቃ ውስጥ የመጀመሪያ ኖታ የምንለው ሙሉ ኖታ እና ሙሉ ዕረፍት ምልክትን ነው
2) ሙሉ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ አራት ምት በድምፅ አለው

3) ሙሉ የዕረፍት ምልክት በውስጡ አራት ምት በዝምታ አለው

4) ግማሽ የሙዚቃ ኖታ በውስጡ ሁለት ምት በድምፅ አለዉ

**መልመጃ 1.1፡ መልስ**

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. እውነት

## 1.2 ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎች እና ውዝዋዜዎችን መለየት

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 6 |

**መግቢያ**

ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎችና ውዝዋዜዎችን ህጻናት እያደረጉ የራሳቸውን አዕምሮ የሚያድሱበት ዘዴ ነው፡፡ የተለያየ እንቅስቃሴዎችን ከውዝዋዜዎች ጋር እያዛመዱ የሚተገበሩበት መንገድ ነው፡፡

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ያሳያሉ
- ስልተ ምትን (ሪትም) ጠብቀው መንቀሳቀስ ያውቃሉ

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

- ተማሪዎች በሙዚቃ ዉስጥ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ምን እንደሆነ እንዲገልፁ አበረታቱ፡፡



ምስል 1.1፡ ደስተኛ የሆነ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ

**መልመጃ 1.2**

ይህን የተግባር መልመጃ በክፍል ላሉ ተማሪዎች እና ለመምህሩ በማሳየት ይመልሱ፡፡

1. ደስተኛ የሆነ የሚለውን መዝሙር በአከባቢያቹ ዜማ በእንቅስቃሴ እና በውዝዋዜ ያሳዩ፡፡
2. በቡድን በቡድን በመሆን ቀድሞ የሚታወቁትን መዝሙሮች ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘምሩ፡፡

## 1.3 ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታዎችን ማየት

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 6 |

**መግቢያ**

ቀለል ያለ እንቅስቃሴዎችንና ውዝዋዜን ህጻናት እያደረጉ የራሳቸውን አዕምሮ የሚያድሱበት ዘዴ ነው፡፡ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ከውዝዋዜዎች ጋር እያዛመዱ የሚተገበሩበት መንገድ ነው፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- ቀለል ያሉ የጨዋታ ዓይነቶች ያውቃሉ
- ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታ ያያሉ

**ማነቃቂያ ጥያቄዎች**

- የጨዋታ ዓይነቶች ዘርዝሩ?
- ትወና ምን ማለት ነው?

**ጠቃሚ መረጃ**

- ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታ የምንለው ትወናን የስው ልጆች በህፃንነታቸው በየአከባቢያቸው የሚጫወቱት ዕቃ ዕቃ ብለው የተለያዩ ቁሶችን በመሰብሰብ ቤት መሰል ነገር አበጅተው በቤት ውስጥ የሚገኘውን ቁሶችን በተለያዩ የወደቁ ዕቃዎችን በመሰብሰብ አበጃጅተው እናት፣አባት፣ልጅ ተባብለው ገፀ-ባህሪያት በመክፈል አባት የአባትን ድርጊቶች እናትም ልጅም በቤት ውስጥ ያዩትን የሚያስመስሉበት ጨዋታ፡፡ ለምሳሌ አባት ሥራ ሄዶ ሲመጣ እናት የምበላ ታቀርባለች ልጅ እጅ ያስታጥባል መሰል

ተግባሮችን በቤታቸው ያዩትን ያስመስላሉ ይህ ደግሞ ቀላል የትወና ጨዋታ ሲሆን ሰዎች መተወንን ከዚሁ ይጀምራሉ፡፡ ራሳቸውን እያወቁ እያደጉ ሲመጡ ድርጊቶቻቸውም እያደገ ይመጣል ፈጠራንም በመጠቀም የተለያዩ ድርጊቶችንም እየጨመሩ ያመጣሉ፡፡

- ለምሳሌ የልጅ ገፀ- ባህሪ የምጫወተው እንድያለቅሰ በማድረግ እናት ስታባብል አባት ከረሜላ ብስኩት ገዛልሃለው ብሎ ወደ ሥራ ሄዶ ሲመለስ መሰሎ ቁሶች በመያዝ ይመጣል ልጅም እንደ ብስኩት እንደ ከሬሜላ በማስመሰል ከበሉ በኃላ የምደሰቱትን የደስታ ስሜት ያንፀባርቃሉ ይህ ልጆች ጨዋታ ለትወና መሠረት ነው፡፡



ምስል 1.1፡ ቀለል ያሉ የትወና ጨዋታ

## መልመጃ 1.3

1. የዕቃዕቃ ጨዋታ በመጫወት ለመምሀራቹ አሳዩ?

## 1.4. ፎቶግራፎችን መመልከት

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 8 |

**መግቢያ**

በዚህ ትምህርት ደለጃ ያሉ  ተማሪዎች የተለያዩ ክንዋኔና ሀሳብ ያላቸው ምስሎች(ፎቶገራፍ) በማሳየት የምን ምስል እንደሆነና ምስሉ ላይ ምን እየተከናወነ እንደሆነ ልጆችን በመጠየቅ ምስሎችን የመለየት ችሎታ፣አከባቢያቸው እንዲረዱ እና ዝንባሌን እንዲያዳብሩ እንዲሁም ሀሳብ የመግለፅ ችሎታቸው ያዳብራል::

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች እና ቅርሶች ምስል ያውቃሉ
- የዕደ-ጥበብ ውጤቶች በማወቅ ያደንቃሉ
- የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳትን ለይተው በማወቅ ያደንቃሉ
- የማጓጓዣ አይነቶችን ይመለከታሉ
- ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች ይመለከታሉ
- የብርሃን ምንጮች ለይተው ያውቃሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ስዕሎች(ፎቶግራፎች)
- ፎቶ ማንሻ (ካሜራ)
- ሞዴል ክፍሎች

**የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች**

- ገለፃ
- ጉብኝት
- ጥያቄና መልስ

➢ የቡድን ስራ

***ጠቃሚ መረጃ***

➢ *መምህር ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ፎቶግራፎችን መመልከትና መለየት ላይ ያተኮረ ስለሆነ ይህ ርዕስ ለማስተማር ከላይ ለተቀመጡ ርዕሶች የሚወክሉ ፎቶዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡*

➢ በዚህ የእድሜና የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በተለያዩ ስልቶች የተነሱ አከባቢያቸው እንዲለዩ እና ተፈጥሮን እነዲያደንቁ ለማድረግና ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ሲሸጋገሩ የራሳቸው ፈጠራ ተጠቅመው ፎቶግራፍ የማንሳት ፍላጎት ወይም ዝንባሌ፣ እውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ የመምህራንና ወላጆች ሃላፊነት ነው፡፡

**ሀ. የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች**

*ተማሪዎች ኢትዮጵያ ሀገራችን ብዙ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች አሉዋት፡፡ ከነዚህ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ለመጎብገኘት ብዙ የውጭ ዜጎች ስለሚመጡ እንደ ገቢ ምነጭ ሆኖው ያገለግላሉ፡፡*

***የማነቃቅያ ጥያቄ***

- *የተፈጥሮ መስህብ ምን ማለት ነው?*
- *ተማሪዎች እስቲ በአከባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎች ለአስተማሪያችሁ ዘርዝሩ?*



ምስል 1.2፡ በኮንታ እና በዳውሮ መሀል የሚገኝ ጨበራ-ጭርጩራ ብሄራዊ ፓርክ



ምስል 1.3፡ በደቡብ ኦሞ ዞን የሚገኝ ማጎ ብሄራዊ ፓርክ

1. ዋካ (ከ እንጨት የምሰራ ቅርፅ)

ዋካ በኮንሶ የሚገኝ ከእንጨት የሚሰራ ቅርፅ ሲሆን በ ዓለም አቀፍ የቅርሳቅርስ መዝገብ ከሰፈሩት የኢትዮጵያ ቅርሶች አንዱ ነው፡፡



ምስል 1.4፡ ዋካ በኮንሶ የሚገኝ ከእንጨት የሚሰራ ቅርፅ

2. ጥያ ትክል ድንጋይ

ጥያ ትክል ድንጋይ በጉራጌ ዞን የሚገኝ ድንጋይ ላይ የተሰሩ ቅርፆች ናቸው፡፡



ምስል 1.4፡ ጥያ ትክል ድንጋይ


**ሐ. ባህላዊ ክንዋኔዎች**

**1. የተለያዩ የቤት አሰራሮች**

**የማነቃቅያ ጥያቄ**

- ቤት ከምን ከምን ይሰራል?
- በአከባቢያችሁ የሚገኙ የቤት አሰራር ዓይነቶችን ዘርዝሩ?

## ባህላዊ የቤት አሰራር



ምስል 1.5፡ ባህላዊ የቤት አሰራር

- *መጀመሪያ የመስርያ ቦታ ማዘጋጀትና በሜትር ለክቶ ቦታውን ማስተካከል*
- *የመስሪያ ቀርከሃ እና የተለያዩ እንጨቶች ማሰባሰብ*
- *ለምሶሶ የሚያገለግል ከፅድ፣ከባህርዛፍ ወይም ኮሶ እንጨት ማዘጋጀት።*
- *የግድግዳ እንጨቶችን ማቆምና በግድግዳ ላይ ማገሮችን መምታት።*
- *(ማሴሪ) ከዚያ መሶሶ ማቆሚያ ቦታ መቆፈርና መሶሶ እንጨቱን ማቆም።*
- *በምሶሶ ላይ ጣሪያ መምታት በጣሪያ ወይም ማገሮችን ወይም የተዘጋጁ ቀርከሃዎችን በገመድ ወይም በወፊቾ ማሰር።*
- *የቤቱ መግቢያ በር ማዘጋጀት።*
- *ለቤቱ ክዳን የሚያገለግሉ ሰንበሌጥ ወይም የስንዴ፣የገብስ የደረቀ ሳር ማሰባሰብና ቤቱን ዝናብ እንዳይገባ አድርጎ መክደን።*
- *በውስጡ የመኝታ ክፍል እና የዕቃ ማስቀመጫ ክፍሎችን መሥራት (የዕቃ ማስቀመጫ መደርደሪያዎችን በመሥራት በደንብ አድርጎ በጭቃ መለሰን።*

**መልመጃ 1.4**

1. ቤት ከምን ከምን ይሰራል?
2. ዋካ(ኮንሶ) ከምን የተሰራ ቅርፅ ነው?
3. ጨበራጨርጨራ ብሄራዊ ፓርክ የት ይገኛል?
4. የተፈጥሮ መስህብ ምን ማለት ነው?

**መልመጃ 1.4፡ መልስ**

1. ከእንጨት፣ከአፈር፣የደረቀ ሳር፣ቆርቆሮ፣ሰሚንቶ፣ብረታብረት ወ.ዘ.ተ.
2. ከእንጨት
3.በኮንታ እና በዳውሮ

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እና የሚያገኟቸውን አከባቢያቸው እንዲለዩ እና ተፈጥሮን እነዲያደንቁ ስዕሎች (ፎቶግራፎችን) በማሳየት እንዲናገሩ /እንዲዘረዝሩ/ እድል መስጠት፤
- አከባብያዊ እና ተፈጥሮኣዊ ገጽታ የሚወክሉ ፎቶዎች በማለት እንዲከፋፍሉ እንዲመድቡ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ምሳሌዎች በማሳየት ማብራሪያ መስጠት፤
- የተለያየ ወንዞች ፎቶግራፎችን በማሳየት የመሰላቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት።

**ክትትል እና የግምገማና ስልቶች**

- ተማሪዎች የተለያየ ወንዞች ፎቶግራፎችን በማሳየት ከተመለከቷቸው ፎቶዎች መካከል ቢያንስ 2 የሚሆኑ ፎቶዎችን መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ተማሪዎች ከተመለከቷቸው አከባቢያዊ እና ተፈጥሮኣዊ ገጽታ ፎቶግራፎችና የሌሎች ወንዞች ፎቶዎች በማየት መለየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ።

**መ. የዕደ-ጥበብ ውጤቶች**

- **የሽመና ስራዎች**

**የማነቃቅያ ጥያቄ**

> ○ አልባሳት ከምን ይዘጋጃሉ?
>
> ○ ሽመና ምንድን ነው?
>
> ○ በአከባቢያችሁ የሚገኙ የሽማ ውጤቶችን ዘርዝሩ?

የሽማ ሥራ ከተለያዩ ክር (ማግ) የሚስራ የሥራ አካል ነው በአከባቢያችን የሚገኙ የጥበብ ልብሶች ከሽማ ሥራ የተገኙ ናቸው፡፡ **ለምሳሌ፡-** የተለያዩ አልባሳቶች፣ሽሚዝ፣ጃፖኒ፣ሱሪ፣ቀሚስ፣ካናቲራ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡



ምስል 1.6፡ የተለያዩ አልባሳቶች

- **የሽክላ ስራዎች**

**የማነቃቅያ ጥያቄ**

- ከ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ?
- ጀበና ለምን ኣገልግሎት ይውላል?

የሸክላ ሥራ ከተለያዩ የአፈር ዓይነቶች ይሰራሉ

**ለምሳሌ፡-** ከጥቁር አፈር፣ከቀይ አፈር ሊሰሩ ይችላሉ

የሸክላ ሥራ ውጤቶች የሚባሉ

ጀበና፣እንስራ፣ገንቦ፣ዋንጫ፣እንክሪት(ማንደጃ) ወ.ዘ.ተ. ናቸው።



እንስራ



ጀበና



እንክሪት



ድስት

ምስል 1.7፡ የሸክላ ስራዎች

## የእንጨት ውጤቶች


**የማነቃቅያ ጥያቄ**

1. እንጨት ከምን እናገኛለን?

| |
|---|
| 2. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የእንጨት ውጤቶችን ዘርዝሩ? |

የእንጨት ውጤቶች ከተለያዩ እፅዋቶች ይዘጋጃሉ፡፡

የእንጨት ውጤቶች የምባሉት በርጩማ፣ጠሬጴዛ፣ወንበር እና ቁምሳጥን በብዛት የምንገለገልባቸው የእንጨት ውጤቶችን ናቸው፡፡ እነዚህን ውጤቶችን ለመቀመጫነት፣ለምግብ ማቅረቢያ እና ለመፃፊያነትም እንጠቀማለን፡፡




ምስል 1.8፡ የእንጨት ውጤቶች

## ሠ. የቤት እና የዱር እንስሳት

- የቤት እንስሳት

የቤት እንስሳት ከሰው ልጅ ተላምደው ቤት ውስጥ የሚኖሩ እና የተለያዩ አገልግሎት እና ጥቅም  የሚሰጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

ፈረስ፣ላም፣ደሮ፣በግ፣ፍየል፣አህያ፣ድመት፣ውሻ ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡

## የዱር እንስሳት

የዱር እንስሳት ማለት ዱር ውስጥ ወይም በመካነ-እንስሳት የሚኖሩ እንስሳት ሲሆኑ፤የቱሪስት መስህብ በመሆን ለአገራችን የገቢ ምንጭ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው።

**ለምሳሌ:**ዝሆን፤ቀጭኔ፣ነብር፣ከርከሮ፣ጉማሬ፣ዜብራ፣አዞ፣ጅብ፣ቆርኪ፣ጎሽ፣ጦጣ፣ የተለያዩ አዕዋፋት ወ.ዘ.ተ.ናቸው።

**ረ. የተለያዩ የማጓጓዣ አይነቶች**

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በአከባቢያችሁ የሚገኙ የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶችን ዘርዝሩ?
- የየብስ፣የአየር እና የባህር የማጓጓዣ ዓይነቶች ዘርዝሩ?

የማጓጓዣ ዓይነቶች በሦስት ይከፈላሉ እነሱም የየብስ፣የባህር እና የአየር ማጓጓዣ ይባላሉ።

- **የየብስ ማጓጓዣ** የሚባሉት እንደነ መኪና፣ሞተር ሳይክል ፣ባስ፣ባጃጅ፣ፈረስ፣ግመል ወ.ዘ.ተ. ናቸው።
- **የባህር ማጓጓዣ** የሚባሉት ጀልባ፣መርከብ ናቸው።
- **የአየር ማጓጓዣ** ደግሞ አውሮፕላን፣ጀት፣ፓራሹት ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

**መልመጃ 1.5**

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ።**

1. አልባሳት ከምን ይዘጋጃሉ?
2. ከ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ?
3. በአከባቢያችሁ የሚገኙ የእንጨት ውጤቶችን ዘርዝሩ?
4. የዱር እንስሳት የሚባሉት እነማን ናቸው?
5. የቤት እንስሳት የሚባሉት እነ ማን ናቸው?

6. ከ ቤት እንስሳት ምን ምን አገልግሎት እናገኛለን?

**ለ. የሚከተለትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ፈረስ የማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡
2. ጀልባ የየብስ ማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡
3. አውሮፕላን የባህር ማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡

**ቀ. ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች**

**የማነቃቂያ ጥያቄ**

- በአከባቢያችሁ የሚገኙ  የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
- ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያ ዓይነቶች ዘርዝሩ?
- ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያ ዓይነቶች ዘርዝሩ?

**ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች**

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የተለያዩ ማህበረሰቦች ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ አንድነታቸውን ለመግለፅ የሚጠቀሙባቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በሀገራችን ሰዎች ለሰርግ፣ ለለቅሶ እና በደቦ ስራ ወቅት ይጠቀሟቸዋል፡፡ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሶስት አይነት ናቸው፡፡እነዚህም

1. **የክር መሳረያዎች፡** ከተለያዩ ክሮች የሚሰሩ ናቸው ለምሳሌ፡ ክራር፣ ማሲንቆ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡
2. **የትንፋሽ መሳሪያዎች፡** በትንፋሽ የሚሰሩ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ለምሳሌ፡ ዋሽንት፣ ዲንኬ፣ ሂጺጼ፣ ዛዬ፣ ፊላ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡
3. **የምት መሳረያዎች፡** በቆዳ እና ከብረት ነክ ቁሶች የሚሰሩ መሳሪዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡ ከበሮ፣ አታሞ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡

### ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች

በአለማችን በርካታ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አሉ፡፡እነዚህም ኪቦርድ፣ ትራምፔት፣ ሀርሞኒካ፣ ድራም፣ ፍሉት፣ ቫዮሊን ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡

**በ. የብርሃን ምንጮች**

ብርሀን ጨለማን በመገርሰስ ነገሮችን እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ብርሀን በተለያየ መንገድ ሊገኝ ይችላል፡፡የብርሀን ምንጮችን ሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ የሚገኙ ብለን ለሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

**ተፈጥሮአዊ የብርሀን ምንጮች፡** የምንላቸው- ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ናቸው፡፡

**ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮች፡** የምንላቸው-አንፖል፣ የእጅ ባትሪ፣ ክብሪት፣ ሻማ፣ ማቀጣጠያ እና እሳት ናቸው፡፡

**መልመጃ 1.5**

**ሀ. የሚከተለትን ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ፡፡**

1. አልባሳት ከምን ይዘጋጃሉ?
2. ከ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሳቁሶች ዘርዝሩ?
3. በአከባቢያቹ የሚገኙ የእንጨት ውጤቶችን ዘርዝሩ?
4. የዱር እንስሳት የሚባሉት እነማን ናቸው?
5. የቤት እንስሳት የሚባሉት እነ ማን ናቸው?
6. ከ ቤት እንስሳት ምንምን አገልግሎት እናገኛለን?

**ለ. የሚከተለትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ፈረስ የማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡
2. ጀልባ የየብስ ማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡
3. አውሮፕላን የባህር ማጓጓዣ ዓይነት ነው፡፡

**መልመጃ 1.5፡ መልስ**

**ሀ. የሚከተለትን ጥያቄዎች በማብራራት መልሱ፡፡**

1. ሸማ ሥራ ከተለያዩ ክር (ማግ) ዓይነቶችን የሚስራ የሥራ አካል ነው፡፡

2. ጀበና፣እንስራ፣ገንቦ፣ዋንጫ፣አንከርት(ማንደጃ) ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡
3. በርጩማ፣ጠሬጴዛ፣ወንበር እና ቁምሳጥን
4. ዝሆን፤ቀጭኔ፣ነብር፣ከርከሮ፣ጉማሬ፣ዜብራ፣አዞ፣ጅብ፣ቆርኪ፣ጎሽ ጦጣ፣የተለያዩ አዕዋፋት ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡
5. ፈረስ፣ላም፣ደሮ፣በግ፣ፍየል፣አህያ፣ድመት፣ውሻ ወ.ዘ.ተ.ናቸው፡፡
6. ለማጓጓዣነት፣ለምግብነት፣የገቢ ምንጭ

**ለ. የሚከተለትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. እውነት
2. ውሸት
3. ውሸት

**መልመጃ 1.6**

1. ባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
2. የክር እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሳርያዎች ዘርዝሩ?
3. ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮችን ዘርዝሩ?

**መልመጃ 1.6፡ መልስ**

1. **ባህላዊ የሙዚቃ መሳርያዎች፡-** ክራር፣ማሲንቆ፣ከበሮ፣ አታሞ፣ዋሽንት፣ ዲንኬ፣ ሂጺጼ፣ ዛዬ፣ ፊላ ወዘተ ናቸው፡፡
2. **ዘመናዊ የሙዚቃ መሳርያዎች፡-** ኪቦርድ፣ ትራምፔት፣ ሀርሞኒካ፣ ድራም፣ ፍሉት፣ ቫዮሊን ወዘተ ናቸው፡፡
3. **የክር መሳሪያዎች፡-** ከተለያዩ ክሮች የሚሰሩ ናቸው ለምሳሌ ክራር፣ ማሲንቆ ወዘተ ናቸው፡፡
4. **የትንፋሽ መሳሪያዎች፡-** በትንፋሽ የሚሰሩ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ለምሳሌ ዋሽንት፣ ዲንኬ፣ ሂጺጼ፣ ዛዬ፣ ፊላ ወዘተ ናቸው፡፡
5. **ተፈጥሮአዊ የብርሀን ምንጮች፡-** የምንላቸው- ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ናቸው፡፡

**ሰው ሰራሽ የብርሀን ምንጮች፡-** የምንላቸው-አንፖል፣ የእጅ ባትሪ፣ ክብሪት፣ ሻማ፣ ማቀጣጠያ እና እሳት ናቸው፡፡

## 1.5. የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን መለየት

የእለት ተእለት ማህበረሰባዊ ክንዋንዎች የምንላቸው በየቀኑ የምንተገብራቸው ከንዋኔዎች ናቸው፡፡ለምሳሌ፡- ገበያ፣ማንበብ፣ጽዳት መጠበቅ፣አብሮ መመገብ፣መጫወት ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 8 |

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን ይለያሉ
- የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን በማየት ያደንቃሉ
- የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን በማየት ያላቸውን ልዩነት ይተነትናሉ

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ስዕሎች /ምስሎች/ (ህፃናትን፣ ተማሪዎችን፣ ቤተሰብን፣ የሚያሳዩ)
- ሞዴል ክፍሎች (የመለማመጃ ክፍሎች)
- ተንቀሳቃሽ ምስሎች/ቪዲዮ/

**የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች**

- ገለፃ
- ጉብኝት
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ስራ

***ማነቃቂያ መሪ ተግባራት***

- በአካባቢያቸው የእለት ተእለት ተግባራትን የሚያሳዩ ምስሎችን እንዲዘረዝሩ ምን ምን አይነት ይዘት (ተግባራዊ) እንቅስቃሴን እንደሚያሳዩ ነፃ ሆነው ከልምዳቸው የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡

***ጠቃሚ መረጃ***

- የእለት ተዕለት ተግባራትን የሚያሳዩ ምስሎች ትኩረት ጠዋት መነሳት፣ እጅና ፊትን መታጠብ፣ ምግብ /ቁርስ/ መመገብ፣ ጥርስን ማፅዳት፣ ፀጉርን ማበጠር፣ ትምህርት ቤት መሄድ፣ አብሮ መጫወት፣ መፅሀፍ ማንበብ፣ ቤተሰብን ማገዝ አከባቢን ማፅዳት ችግኝ መትከል በሚሉ ትረካዎች ላይ ያተኮረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- በዚህ የእድሜና የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በተለያዩ ስልቶች የተሰሩ እና የዕለተ ተዕለት ተግባራትን የሚያሳዩ ወይም የሚወክሉ ምስሎችን እንዲለዩ ለማድረግና ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ሲሸጋገሩ በራሳቸው ፈጠራ አስመስለው የመስራት ዝንባሌ፣ እውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ የመምህራንና ወላጆች ሃላፊነት ነው፡፡

***የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች***

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እና የሚያገኟቸውን የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን እንዲናገሩ /እንዲዘረዝሩ/ እድል መስጠት፤
- ተማሪዎች ከሰጧቸው የዕለት ተእለት ተግባራት ምስሎችን መልስ በመነሳት የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎች በማየት እንዲከፋፍሉ እንዲመድቡ ማድረግ እንደሁም በጾታ ወንድ ሴት፣ በእድሜ ህፃናት፣ ወጣትና ሽማግሌ፣ በስራ ነጋዴ፣ ገበሬ፣ መምህር፣ ሀኪም፣ ወዘተ በማለት ማብራሪያ መስጠት፤
- የተለያየ የእድሜ፣ የስራና የፆታ ምሳሌ የሚሆኑ ምስሎች በማየት የመሰላቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት፡፡
- ከላይ የተቀመጡ ምስሎችን ማየት የመሰላቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት፡፡

- ተማሪዎች ከሰጧቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎችን መልስ በመነሳት የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎች በማለት እንዲከፋፍሉ እንዲመድቡ ማድረግ፡፡

### 1.5.1 ንጽህናን መጠበቅ

አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ጠዋት ከእንቅልፉ እንደተነሳ ፊቱን ይታጠባል ፣ጥርሱን ይቦርሻል፣ ፀጉሩን ያበጥራል የራሱን ንጽህና ከጠበቀ በኋላ የተኛበትን አልጋ በማንጠፍ ቤቱን እና አከባቢው በመጥረግ ንጽህና ይጠብቃል፡፡



ምስል 1.9፡ ልጆች አካባቢያቸውን ሲያፀዱ

### 1.5.2 እጽዋትን መንከባከብ

አበባና አበበ የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡አበበ እጽዋትን መትከል ይወዳል፡፡አበባ ደግሞ አበበ የተከላቸውን እጽዋቶች ውሀ በማጠጣት ትንከባከባቸዋለች፡፡አበባና አበበ በትምህርት ቤታቸው የተለያዩ የእጽዋት

አይነቶችን በመትከል የትምህርት ቤቱን ግቢ ጽዱና ማራኪ እንዲሆን አድርገዋል፡፡



ምስል 1.10፡ ልጆች በጋራ ችግኝ ሲተክሉ

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- በዕለት ተዕለት ተግባራት ከተመለከቷቸው ምስሎች መካከል 3-5 የሚሆኑ ምስሎችን መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፡፡
- ተማሪዎች ከተመለከቷቸው የዕለት ተዕለት ተግባራት ምስሎች መልስ በመነሳት የዕለት ተዕለት ተግባራት መመደባቸውን (መለየታቸውን) በምልከታ ማረጋገጥ፡፡

**ማጠቃለያ**

- በመጀመሪያ ኖታ የምንለው የሙዚቃ ፊደላትን ነዉ፡፡ ሙሉየሙዚቃ ኖታ በውስጡ 4 ምት ያለው ሲሆን በጊዜ ዋጋ ከሁለት ግማሽ ኖታዎች

ጋር እኩል ነው።ግማሽ የሙዚቃ ኖታ ማለት ሁለተኛው የኖታ ዓይነት ሲሆን በውስጡ ሁለት ምት አለው።

- የቤትንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ከበሽታ ይከላከለናል።
- የተፈጥሮ መስህብ ቦታዎችን ለመጎብኘት ብዙ የውጭ ዜጎች ስለሚመጡ እንደ ገቢ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ።

**ማጠቃለያ መልመጃ**

1. የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን ዘርዝሩ?
2. የዱር እና የቤት እንስሳት የሚባሉ እነ ማን ናቸው?
3. የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን ዘርዝሩ?

**መልስ**

1. የሸማ ስራዎች፣የሸክላ ስራዎች፣የእንጨት ውጤቶች
2. ዝሆን፤ቀጭኔ፣ነብር፣ከርከሮ፣ጉማሬ፣ዜብራ፣አዞ፣ጅብ፣ቆረኪ፣ጎሽ ጦጣ፣የተለያዩ አዕዋፋት ወ.ዘ.ተ.ናቸው።
3. **የየብስ ማጓጓዣ** የሚባሉት እነደነ መኪና፣ሞተር ሳይክል ፣ባስ፣ባጃጅ፣ፈረስ፣ግመል ወዘተ ናቸው።

**የባህር ማጓጓዣ** የሚባሉት ጀልባ፣መርከብ ናቸው።

**የአየር ማጓጓዣ** ደግሞ አውሮፕላን፣ጀት፣ፓራሹት ናቸው።

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1. ሙዚቃ እንቅስቃሴዎችን ከውዝዋዜዎች ጋር እያዛመዱ የሚተገብሩበት መንገድ ነው።
2. ቀለል ያሉ እንቅስቃሴዎችንና ውዝዋዜን ህጻናት እያደረጉ የራሳቸውን አዕምሮ የሚያድሱበት ዘዴ ነው።

**እውነት ወይም ሐሰት  መልስ**

1. እውነት
2. እውነት

| ምዕራፍ 2 | ፈጠራዊ አገላለፅ |
|---|---|

| ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 27 |
|---|---|

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- ❖ የሙዚቃ ኖታዎችን ተጠቅመው የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡
- ❖ ቀላል የትወና ጨዋታ ይጫወታሉ፡፡
- ❖ ቀላል መስመሮችን ተጠቅመው አከባቢያቸው ላይ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በወረቀት ላይ ይስላሉ፡፡

## 2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መጫዋት

| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 11 |
|---|---|

**መግቢያ**

በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ የየራሳቸው የሆነ የጊዜ ዋጋ  ያላቸው የሙዚቃ ኖታዎች እንዳሉ በምዕራፍ አንድ ላይ የተመለከቱትን በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች እንድያነቡ ማደረግ (ማሳየት)፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- የሙዚቃ ኖታዎችን ተጠቅመው የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን አጻጻፍ ይገልፃሉ፡፡
- የሙዚቃ ኖታዎችን ይለማመዳሉ፡፡

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

- **መምህር፡** ተማሪዎች የሙዚቃ ኖታዎችን ማጫወት ምን እንደሆነ እንድያብረሩ ያበረታቱ፡፡

ስለዚህ በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉ ሕፃናት ስለ ሙዚቃ ኖታዎች በደንብ እንዲረዱ የተለያዩ ምልክቶችን በመጠቀም ስለ ጊዜ ዋጋና ስለ ዕረፍት ዋጋ በማስተማር ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

ወረቀት

እርሳስ

**ጠቃሚ መረጃ**

በዚህ ዕድሜ ደረጃ ላሉ ተማሪዎችስለሙዚቃጠቀሜታ ወይም ስለ ሙዚቃ ኖታዎች ምንነት የሙዚቃ እውቀት ያለው ሰው ሁሉ ከወላጆችና ከመምህራን ጎን በመሆን ለሕፃናቱ ዝንባሌ እውቀት ክህሎት እንድያዳብሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡


**ክትትል እና ግምገማ**

- የሙዚቃ ኖታዎችን እና የዕረፍት ምልክቶችን በአግባቡ መለየታቸውን በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡


- የሙዚቃ ኖታዎቹን በትክክል የጊዜ ዋጋቸውን ጠብቆ ማንበባቸውንወይም ማንበብ መቻላቸውን በመመልከት ማረጋገጥ፡፡
- የእያንዳንዱንኖታዎችበትክክለኛው ሪቲም (ስልተምት) በመጠበቅ ማንበባቸውን ማረጋገጥ፡፡
- የተለያዩ የህፃናትን ጨዋታዎች (መዝሙሮችን) ስለ መዘመራቸው ማረጋገጥ፡፡

**መልመጃ 2.1**

1) የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች ስም ፃፍ

ሀ.  ______________________

ለ.  ______________________

ሐ.  ______________________

መ.  ______________________

ሠ.  ______________________

2) የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች የጊዜ ቆይታ በቁጥር ያስቀምጡ

ሀ.  ________________________

ለ.  ________________________

ሐ. O ________________________

መ.  ________________________

ሠ.  ________________________

**መልመጃው 2.1፡ መልስ**

1. <u>የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች ስም ፃፍ</u>

   ሀ. ግማሽ ኖታ

   ለ. ሙሉ እረፍት ምልክት

   ሐ. ሙሉ ኖታ

   መ. ግማሽ እረፍት ምልክት

   ሠ. ግማሽ ኖታ

2. <u>የእነዚህን የሙዚቃ ኖታዎች የጊዜ ቆይታ በቁጥር ያስቀምጡ</u>

   ሀ. 2

   ለ. 4

   ሐ. 4

   መ. 2

   ሠ. 2

## 2.2 ቀለል ያሉ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 8 |

### ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ

- ❖ ልጆች እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜን ይለያሉ
- ❖ ሕፃናት ስለደስታ፣ስለ እናት እና ስለ ቤተሰብ አባላት በእንቅስቃሴና ውዝዋዜ ይዘምራሉ
- ❖ መዝሙርን በመዘመር ይደሰታሉ

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

- ❖ ተማሪዎች በሙዚቃ ዉስጥ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ምን እንደሆነ እንድገልፁ አበረታቱ፡፡

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግባዓቶች**

- የሕፃናት መዝሙሮች እና
- የመጫወቻ  ቦታ(ስፍራዎች

**ጠቃሚ መረጃ**

- በዚህ የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ ሕፃናት በእንቅስቃሴ (በውዝዋዜ) መሐል ያለውን ልዩነት መረዳትና በአከባቢያቸው የሚመለከቱትን ነገሮች (በቤተሰቦቻቸው) ውስጥ ያለውን ነገሮች በመዝሙር መልክ በእንቅስቃሴ እና በውዝዋዜ አስመስሎ የመዘመር ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ፡፡

**ክትትል እና ግምገማ**

- ስለ ቤተሰብ በተለያዩ እንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ መዘመራቸውን ማረጋገጥ ሲንቀሳቀሱ እንደይወድቁ መምህራን(የልጆች ሞግዚቶች) እንድጠብቁ መናገር

## 2.3 ቀላል የትወና ጨዋታዎችን መጫወት

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 9 |

**መግቢያ**

ቀላል የትወና ጨዋታ የምንላቸው ትወና ልጆች በልጅነታቸው የቤተሰብን ገፀ-ባህሪያት በመከፋፈል እያስመሰሉ ይጫወታሉ፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

| |
|---|
| **ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ**<br>1. ቀላል የትወና ጨዋታ ይጫወታሉ፡፡<br>2. የቤተሰብን ገፀ- ባህሪያት ወክለው ይጫወታሉ፡፡ |

**ጠቃሚ መረጃ**

እናት አባት ልጅ ተባብለው የአባትን የምተውነው አባት ከሥራ ስመለስ ፤ቤት ውስጥ የምናገራቸው የምያደርጋቸው ድርጊቶች እያስታወሱ ይተውናሉ (ያስመስላሉ) አባት ከሥራ ስመጣ እናት ምግብ ታቀርባለች ልጅ እጅ ያስታጥባል መሰል ድርጊቶች በማስታወስ ያስመስላሉ፡፡ ይህ የማስመሰል ጨዋታ አድጎ አለባዊያን ተጨምሮበት የትወና መንገዶች (ቴክኒኮች) ተጨምረውበት እስከ ተውኔት (ትያትር) ድረስ ያድጋሉ መሰረቱ የማስመሰል የልጆች ጨዋታ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች**

- ገለፃ
- ጉብኝት
- የቡድን ስራ

**መልመጃ** 2.2

1. ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው አብልጦ ምንን እንደምወዱ ጠይቀው እንድያስመስሉ ያደርጉ፡፡
2. ተማሪዎች ቡድን በቡድን በመሆን የእናት የአባት የልጅ ገፀ-ባህሪያትን በመከፋፈል እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

## 2.4. ቀላል መስመሮች በመጠቀም ንድፎችን መለማመድ

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 12 |

**መግቢያ**

በዚህ ትምህርት ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ቀለል ያሉ ንድፎች እና መስመሮች ተጠቅመው በምዕራፍ አንድ የተመለከትዋቸው ምስለችን ወረቀት ላይ

ይስላሉ፣በተጨማሪም ባለ ሁለት አውታር ቅርፆችን በመገጣጠም ቀለል ያሉ ስዕሎችን በመስራት ክህሎታቸው ያዳብራሉ፡፡

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

| |
|---|
| **ተማሪዎች ይህን ርዕስ ከተማሩ በኋላ**<br>1. የተለያዩ መስመሮች ዓይነቶች ያውቃሉ፡፡<br>2.ቀላል መስመሮችን ተጠቅመው አከባቢያቸው ላይ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በወረቀት ይስላሉ፡፡<br>3.ባለ ሁለት አውታር ቅርፆችን በመገጣጠም ቀለል ያሉ ስዕሎችን ይስላሉ፡፡ |

## ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- እስራስ፣ወረቀት፣ማርከር፣ባለቀለም ጠመኔ
- የተለያዩ መስመሮች ዓይነቶች የሚያሳዩ ስዕሎች
- ሞዴል ክፍሎች

## የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች

- ገለፃ
- ጉብኝት
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ስራ


## ጠቃሚ መረጃ

- መምህር ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ቀለል ያሉ ንድፎች እና መስመሮች አከባቢያቸው ላይ የሚገኙ ቁሳቁሶች መሳል ላይ ያተኮረ ስለሆነ መምህር እነዚህ ርዕሶች የሚወክሉ ስዕሎችን በማሳየት በተጨማሪም ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመሳል ማሳየት አስፈላጊ ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- አከባብያዊ እና ተፈጥሮኣዊ ገጽታ የሚወከክሉ ፎቶዎች በማለት እንዲከፋፍሉ እንዲመድቡ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ምሳሌዎች በማሳየት ማብራሪያ መስጠት፤
- የተለያዩ የመስመሮች ዓይነቶችን በማሳየት በራሳቸው እነዲሰሩ እድል መስጠት።

**መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ**




ምስል 2.1መስመሮች በመጠቀም መቸክቸክ

**መልመጃ 2.3**


1. አግድምና ቁልቁል ቀጥታ መስመሮችን በወረቀት ላይ አስምሩ?
2. የተለያዩ መስመሮችን ተጠቅማችሁ ወደብዙ አቅጣጫ ቸክችኩ?

## የተለያዩ የመስመር አይነቶች





ምስል 2.2፡ የተለያዩ የመስመር አይነቶች


ባለ ሁለት አውታር ቅርፆች በመገጣጠም ተማሪዎች እንዲሰሩ ማድረግ፡፡



ምስል 2.3፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእራስ በመገጣጠም ታክሲ መሳል




ምስል 2.4፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእራስ በመገጣጠም ክራር መሳል




ምስል 2.5፡ ዝርግ ቅርፆች እርስ በእራስ በመገጣጠም ጎጆ ቤት መሳል

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- ተማሪዎች የተለያየ ወንዞች ፎቶግራፎችን በማሳየት ከተመለከቷቸው ፎቶዎች መካከል ቢያንስ 2 የሚሆኑ ፎቶዎችን መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፡፡
- ተማሪዎች ከተመለከቷቸው አከባብያዊ እና ተፈጥሮኣዊ ገጽታ ፎቶግራፎችና የሌሎች ወንዞች ፎቶዎች በማለት መለየታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፡፡




ምስል 2.12፡ በቀላል መስመሮችን እና ቅርፆችን በመገጣጠም ዓሣ መሳል




ምስል 2.6፡ በቀላል መስመሮች እና ቅርፆች በመገጣጠም ዶሮ መሳል

# ማጠቃለያ

- ሙሉ የሙዚቃ ኖታ እና ሌሎችንም የሙዚቃ ኖታዎች እና የእረፍት (ድምፅ አልባ) የሙዚቃ ምልክት እንዴት በምልክት ማንበብ እንደምንችል እንመለከታለን ሁሌም ልጆች ከእንቅስቃሴ እና ውዝዋዜ ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ማለትም ልጆች ማንኛውም ነገር ለመግለፅም ሆነ ለመረዳት በእንቅስቃሴ (ውዝዋዜ) ሲሆን ቶሎ የመረዳት አቅም አላቸው፡፡
- የመስመር መጀመርያ ነጥብ ነው፡፡ አንድ ነጥብ ከሌላኛው ነጥብ ጋር ስናገናኝ መስመር እንሰራለን፡፡
- ንድፍ ማለት እርሳስን ተጠቅመን አንድ መስመር ከሌላ መስመር እየቀጣጠልን ወረቀት ላይ የምንሰራቸው የጥበብ ሥራዎች ንድፍ ይባላሉ፡፡

**የማጠቃለያ መልመጃ**

1. ሙሉ የሙዚቃ ኖታ እና ግማሽ የሙዚቃ ኖታን ከነ የእረፍት ምልክታቸዉ ያሳዩ
2. ንድፍ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ንድፍ ለመስራት የሚስፈልጉ ግብአቶችን ዘርዝሩ?
4. መስመር ማለት ምንድነው?

**መልስ 1.4**

1. O ሙሉ ኖታ-   ▔ ሙሉ የእረፍት ምልክት

   𝅗𝅥 ግማሽ ኖታ   ▬ ግማሽ የእረፍት ምልክት
2. ንድፍ ማለት እርሳስን ተጠቅመን አንድ መስመር ከሌላ መስመር እየቀጣጠልን ወረቀት ላይ የምንሰራቸው የጥበብ ሥራዎች ንድፍ ይባላሉ፡፡
3. እርሳስ፣ወረቀት፣ማርከር፣ባለቀለም ጠመኔ ወ.ዘ.ተ
4. አንድ ነጥብ ከሌላኛው ነጥብ ጋር ስናገናኝ መስመር እንሰራለን፡፡

| ምዕራፍ 3 | ሀገረ-ሰባዊ ምልከታዎች |
|---|---|

| ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 20 |
|---|---|

**መግቢያ**

ባህል በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የሚፈጠር የተግባቦሽ ዘይቤ ነው፡፡ ባህል የአንድ ማህበረሰብ የማንነቱ መገለጫ ማለትም የአመጋገብ ስርዓት፣የአለባበስ ስርዓት፣ ባህላዊ ሙዚቃው እና ባህላዊ ጭፈራው በአጠቃላይ  የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ በዚህ መሰረት

- ባህል ማህበረሰቡ በሚያራምደው የአዲስ ትዉልድ ትምህርትና አስተዳደግ እንዲሁም ማህበራዊ እዉቀት እንዴት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እንደሚተላለፍ የመወሰን ድርሻ አለው፡፡ በዚህ መልኩ ባህል ስነ ትምህርትን ፣ሃይማኖትን፣ሳይንስን፣ ኪነ ጥበብን፣ሥነ ቃልንና የማህበራዊ ኑሮ አወቃቀርን ይወስናል፡፡
- በየአካባቢው ያሉ ሁሉም ባህሎች ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚያበረክቱት የራሱ የሆነ አሰተዋጽኦ አላቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ይዘት ላይ ባህልን ከባህል ተማሪዎች እንዲያወዳድሩ ሳይሆን የሚሰሟቸውን ሙዚቃዎች፣ የሚለብሷቸውን ባህላዊ አልባሳት በአጠቃላይ የሚያዩትን ባህል አድናቆትን እንዲሰጡ ነው፡፡

## ከመዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

| |
|---|
| **ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ**<br>❖ በአከባቢያቸው የሰሙትን ሙዚቃ እየዘመሩ ውዝዋዜ ያደርጋሉ<br>❖ ተዛማች ታሪኮችን ከሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ጋር ያዛምዳሉ<br>❖ ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃንና ውዝዋዜን ይለያሉ<br>❖ የብሔር ብሔረሰቦችን ሙዚቃ ይጫወታሉ<br>❖ ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ያውቃሉ፡፡<br>❖ የቤተሰቦቻቸውን እና የጓደኞቻቸውን የልብስ ቀለማት (የሀገራቸውን የክልላቸውን የሰንደቅ አላማ ቀለማት ለይተው ያውቃሉ) |

## 3.1 ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 6 |

### መግቢያ

ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ (ባህል) በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚፈጠር ተግባቦት ዘይቤ ነው፡፡ ይህ ዘይቤ በማህበረሰቡ በጎ ስነ-ምግባር የጋራ ዕሴቶች፣እምነቶች፣ፅንሰ ሃሳቦችን ይወስናል፡፡ በዚህ መሰረት ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ በሕብረተሰቡ ውስጥ በሚያላምደው የአዲስ ትውልድ ትምህርትና አስተዳደግ እንዲሁም ማህበራዊ እውቀት እንዴት በሙዚቃ ከትውልድ ወደ ትውልድም እንደሚተላለፍ የመወሰን ድርሻ አለው፡፡ በሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ (እንቅስቃሴ) ባህልን፣ሥነ ትምህርትን፣ኃይማኖትን፣ሳይንስን፣ኪነ ጥበብን፣ሥነ ቃልንና የማህበራዊ ኑሮ አወቃቀርን ማሳየት ይችላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ክፍል ደረጃ ያሉ ሕፃናት ስለ ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ እንዲያውቁ ታስቦ የተመረጡ ይዘቶችን በማስተማር ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**

- ልጆች ስለ ሀገራቸው ባህል ያውቃሉ
- ልጆች ባህላዊ ጨዋታወችን ይጫወታሉ
- ልጆች ባህላዊ ሙዚቃን በውዝዋዜ ያሳያሉ

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

1. ተማሪዎች ስለ ሀገረ - ሰባዊ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ምን እንደሆነ እንዲገልፁ ማበረታታት፡፡

## የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

- ገለፃ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ሥራ
- የክፍል ሥራ
- የቤት ሥራ
- ውይይት
- ጉብኝት
- የተግባር ሥራ

## ለዕርሱ የሚያስፈልጉ ግባዓቶች

- ለባህላዊ ዘፈኖች የሚያገለግሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች
- አልባሳቶች
- በካሴት የተቀዱ ባህላዊ ዘፈኖች

## ጠቃሚ መረጃ


- ተማሪዎች ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ ውስጥ እንድሳተፉ ለማድረግ አካላቸውን እንድያንቀሳቅሱ እና የውዝዋዜ ቅንጅት እንዲኖራቸው ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡

➤ የሀገራቸውን (የአከባቢያቸውን) ባህላዊ ዘፈኖችን እና ጭፈራዎችን ማወቅ በራስ መተማመንን ከማጎልበቱም በላይ ደስታን እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ በአከባቢያቸው ያለውን ባህላዊ ጭፈራ እና ውዝዋዜን በምገባ ግንዛቤ ማስጨበጥ አስፈላጊ ነው፡፡

## ክትትል እና ግምገማ

➤ ልጆች በህላዊ የሙዚቃ ጨዋታዎችን ምንነት አምድገልጹ ጥያቄ መጠየቅ
➤ ባህላዊ ጨዋታዎችን በውዝዋዜ መጫወታቸውን በመመልከት ማረጋገጥ
➤ ባህላዊ የሙዚቃ ጨዋታዎችን ማድነቃቸውንና በንቃት መሳተፋቸውን በመመልከት ማረጋገጥ

## ለምሳሌ እነዚህን ምስሎች እንመልከት



ምስል 3.1፡ የቤንሻንጉል አከባቢ የሙዚቃ መሣሪያ



ምስል 3.2፡ የኮንሶ ባህላዊ ጭፈራ



ምስል 3.3፡ የሐመር የሴቶች አለባበስ እና ጭፈራ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ በሚገኙ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተሰራ መዝሙር

**እኛም አለን ሙዚቃ**

እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ

ዋሽንታችን ላ ላ ላ ላ ላ

ካሳችን ላ ላ ላ ላ ላ

ድንኪያችን ፓምፓምፓምፓምፓም

አታሞችን ድንድንድንድንድን

ሎላታችን ላ ላ ላ ላ ላ



ምስል 3.4፡ ሎላታ



ምስል 3.5፡ ካሳ




ምስል 3.6፡ ዋሽንት



ምስል 3.7፡ አታሞ

**ተረት ተረት (ሞኙ ቀበሮ)**

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ቀበሮ አንድ ትንሽ ግልገል አየና ቀስ ብሎ ወደ እሷዋ ተጠጋና ለግልገሏ እግሯን አስሮ ለመብላት ሲል "እኔን ልትበላኝም ልትገለኝም ትችላለህ የእኔ የመጨረሻ ቃል እባክህ ስማኝ" አለችው፡፡ "ያንቺ ቃል ምንድ ነው?" በማለት ጠየቃት፡፡ እሷዋም "እባክህ አንተ ዋሽንት ብትጫወትልኝ ደስ ብሎህ ትባላኛለህ" በማለት ነገረችው፡፡እሱም ደስ ብሎት ዋሽንቱን በማምጣት አንተ የዋሽንቱን በሚትጫወትበት ጊዜ በጣም ደስ ይላል አለችው ያሞኝ ቀበሮ ዋሽንቱን ድምፁን ከፍ በማድረግ መንፋት ጀመረ የዋሽንቱን ድምፅ የሰማው የበግ ጠባቂ የራሱን ሁለት ውሻዎችን ጠራቸው ውሻዎችም ያ ሞኝ ቀበሮ ያለበት ደርሶ ግልገሏዋን ከሞት አተረፉዋት፡፡ብልህና ብልጥ የሆነች ግልገል እየተደሰተችና እየሳቀች ተመለሰች፡፡



የዚህ ተረት ቁም ነገር በዚህ ዘመን ብልህና ቁም ነገረኛ መሆን እንዳለብን ይገልፃል፡፡

**መልመጃ 3.1**

1. ሀገረ-ሰባዊ ሙዚቃ ወይም ውዝዋዜ ማለት ምንማለት ነው?
2. ሀገረ-ሰባዊ ማለት ምን ማለት ነው?
3. በአከባቢያችሁ በሃዘን ጊዜ የምጠቀሙት የሙዚቃ መሣሪያ ግለፅ
4. በደቡብ ብሄር ብሔርሰቦች ውስጥ በሚገኙ የሙዚቃ መሣሪዎች የተሰራ መዝሙር በሚለው የግጥሙን ርዕስ ግለፅ
5. ለግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት
6. ሞኙ ቀበሮ ለመብላት ያለው ማንን ነው?
7. ትንሽ ግልገል ምን ዓይነት ጥያቄ አቀረበች?
8. ሞኙ ቀበሮ የተጠቀመውን የሙዚቃ መሣሪያ ግለፅ
9. የዚህ ተረት ዋና ዓላማ ምንድነው?

**መልመጃ 3.1፡ መልስ**

1. በአንድ አከባቢ (ሀገር) የሚከናወኑ (የክንዋኔዎች) መገለጫን በሙዚቃ እና በውዝዋዜ በማዋዛት የሚከናወን ነው፡፡
2. ሀገረ-ሰባዊ ማለት የአንድ አከባቢ ባህላዊ (እምነት) ማለት
3. የዚህ ጥያቄ መልሶች በመምህሩ ይመለሳሉ
4. እኛም አለን ሙዚቃ
5. ስድስት ስንኞች አሉት
6. ትንሻዋን ግልገል
7. ዋሽንት ብትጫወትልኝ ደስ ይለኛል
8. ዋሽንት
9. በዚህ ዘመን ብልህና ቁም ነገረኛ መሆን

## 3.2 ተዛማጅ ታሪኮች

| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 5 |
|---|---|

### መግብያ

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ በአካባቢያቸው ካሉ ታሪኮች በመነሳት ታሪክ እንድያውቁ የተለያዩ ታሪኮችን እንዲያነቡ እና እንዲሰሙ ወይም ፎቶግራፎችንና ስዕሎችን በማሳየት ታሪክን የማወቅ ዝንባሌ እና ፍላጎቱ እንዲኖራቸው ተዛማች ታሪኮች ከአካባቢያቸው እስከ ሃገራቸው ድረስ ያሉ በየዘመኑ የተከናወኑ ክንዋኔዎች፣ በተለያዩ ሙያዎች የተሰማሩ የታዋቂ ሰዎች፣የሀገርና ፣የቦታ ስሞችን ወዘተ ማዋቅ አለባቸው፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

| **ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**<br><br>1. አከባብያዊ ጥበቦችን በመጠቀመም መዝሙሮች፣የተውኔት ገጸበህርያት በውዝዋዜ ያውቃሉ፡፡<br>2. ተዛማጅ ታሪኮች እና ተረቶችን ያውቃሉ፡፡ |
|---|

### የእርቅ ስነ-ስርዓት

በጋሞ ዞን የሚኖሩ ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የእርቅ ስነ ስርዐት አላቸው፡፡በደል ያደረሰው አካል ለሀገር ሽማግሌዎች ስለ ችግሩ ያስረዳል፡፡የሀገር ሽማግሌዎችም ዱቡሻ በሚባል አደባባይ ላይ የበዳይ እና ተበዳይ ወገንን ይሰበስባሉ፡፡የሀገር ሽማግሌዎች ፃምፓራ የሚባል ጦር መሳይ መሳሪያ በማቆም እረጥብ ሳር ይዘው የተበዳይ ወገንን ለእርቅ ይጠይቃሉ ፡፡የእናንተ መበደል የእኛም በደል ነው ታሳ ታና ሞ እኔን እርቅ ማውረድ ደግሞ ከጥንት አባቶቻችን የወረስነው ባህል ነው እባካችሁ እረቁን ተቀበሉ ብለው ይማጸናሉ፡፡ተበዳዮችም

ለሽማግሌዎቹ እሺ እርቁን እንቀበላለን ብለው ይገልጻሉ፡፡ከእርቁ በኃላ በበዳይ ቤት ለተበዳዮች ግብዣ ያደርጋሉ፡፡ በዳይና ተበዳይም በአንድ ቅል ፋርሶ ወይም ቦርዴ ይጠጣሉ በማህላቸውም ሰላም ይወርዳል፡፡

*ጠቃሚ መረጃ ለመምህሩ*

- *ታዋቂ ታሪኮች ከአካባቢያችን እስከ ሃገራችን ድረስ ያሉ በየዘመኑ የተከናወኑ ክንዉኖች፣ በተለያዩ ሙያዎች የተሰማሩ የታዋቂ ሰዎች፣የሀገርና ፣የቦታ ስሞችን ወዘተ ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ ጥቂቶቹን ብንመለከት፡-*
- *መምህር ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ በአካባቢያቸው በክልላቸው እንዲሁም በሀገራቸው የሚያዉቁትን የሰዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት የተከናወኑ ክስተቶችን፣ የቦታ እና የሀገር ታሪኮችን ወዘተ የተለያዩ የታሪክ መጽሃፍትን በመጠቀም ለልጆቹ ቀለል ባለ መልክ መንገር ያስፈልጋል፡፡*
- *በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ካሉ ታሪኮች በመነሳት ታሪክ እንዲያዉቁ የተለያዩ ታኮችን መንገርና ታሪኩን የሚያሳይ ፎቶግራፎችንና ስዕሎችን ማሳየት እዉቀቱና ታሪክን የማወቅ ዝንባሌ እና ፍላጎቱ እንዲኖራቸው ማድረግ የመምህራንና ወላጆች ሃላፊነት ነው፡፡*

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- *ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን የተለያዩ ታሪኮች እንዲናገሩ እድል መስጠት፤*
- *ከዚህ በመነሳት ታሪኮችን ቀለል ባለ መልክ ለህጻናት በሚሆን መልክ ወይ በተረት መልክታሪኮችን መንገር፡፡*
- *የታሪኩን ጭብጥ ሃሳብ ወይም ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት ለልጆቹ መንገር፡፡*

- በዚህ ይዘት ስር የተቀመጡ መዝሙሮችን ከዚህ በፊት በተቀመጠው የመዝሙር አተናን ዘዴ በመጠቀም እንዲለማመዱ ማድረግ።
- መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት ለልጆች መንገር
- መዝሙሩን ከዘመሩ በኋላ ታሪኩን መሰረት በማድረግ በትያትር እንዲጫወቷቸው ማድረግ።
- የሰሩትን ስራ በማወዳደር የተሻለ የሰሩትን ማበረታታት

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- ተማሪዎች ከተማሯቸው ታሪኮች ቢያንስ አንዱን እንዲናገሩ በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ።
- ተማሪዎች በፎቶ ግራፍ ወይም በስዕል ካዩት ታሪክ በመነሳት ስለ ተግበራቶቻቸው እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።

## 3.3 ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቀለማት እና ትወና ከባህላዊ ምልከታዎች አኳያ

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 15 |

**መግቢያ**

ማህበረሰብ ማለት በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ሲሆኑ ተመሳሳይ የሆነ የአመጋገብ ስርዓት፣የባህል፣የቋንቋ፣የአለባበስ ስርዓት፣የኑሮ ሁኔታ ወ.ዘ.ተ.የሚጋሩ ህዝቦች ናቸው።

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ቀለማት እና ትወና ከባህላዊ ምልከታዎች አኳያ የሚለው ይመለከታሉ።

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

| **ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ ኃላ** |
|---|
| ➢ የአከባቢያቸውን ባህልና ወግ ይለያሉ<br>➢ ልጆች እንደ አከባቢያቸው ባህልና ወግ ሙዚቃን ይጫዋታሉ።<br>➢ ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ያውቃሉ።<br>➢ የቀለም አይነቶች ያውቃሉ።<br>➢ የቤተሰቦቻቸው እና የጋደኞቻቸው የልብስ ቀለማት (የሀገራቸው የክልላቸው የሰንደቅ አላማ ለይተው ያውቃሉ። |

### 3.3.1. ሙዚቃ እና ውዝዋዜ ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

ሙዚቃ እና ውዝዋዜ በተለያዩ ማህበረሰብ ከባህላዊ ምልከታ አንፃር ስንመለከት ሁሉም ሙዚቃን እንደ እምነታቸው እንደ አከባቢያቸው ባህልና ወግ የሁሉም አጠቃቀም የተለያየ መሆኑን እንመለከታለን።

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

1. ልጆች ስለ ሙዚቃ እና ስለ ውዝዋዜ ከባህላዊ ምልከታ አኳያ ያለቸዉን እዉቀት ነፃ ሆነዉ ከልምዳቸዉ የሚያዉቁትን ነገር እንድነገሩ ማበረታታት።

### 3.3.2. ቀለማት ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

ማህበረሰብ ማለት በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ሲሆኑ ተመሳሳይ የሆነ የኣመጋገብ ስርዓት፣የባህል፣የቋንቋ፣የኣለባበስ ስርዓት፣የኑሮ ሁኔታ ወ.ዘ.ተ.የሚጋሩ ህዝቦች ናቸው።

ስለዚህ መምህር በዚህ ርዕስ በማህበረሰብ ውስጥ ያለው የቀለማት ትርጉም ከባህላዊ ምልከታዎች አካያ ለተማሪዎች መግለፅ እና ማሳየት።

ቀለማት እንደየማህበረሰቡ የተለያየ አመለካከት አና ትርጉም አላቸው።

**ለምሳሌ፡** በአንድ አከባቢ ጥቁር ቀለም የሃዘን መገለጫ ሲሆን በልላኛው ማህበረሰብ ደግሞ ጥቁር ቀለም የደስታ ወይም የጥሩ ነገር ተምሳሌት ሁኖ ልናገኘው እንችላለን፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች ቀለማት እንደየባህሉ እና እንደየማህበረሰቡ የተለያየ ትርጉም እና አመለካከት አላቸው፡፡ ሰዎች ቀለሞችን ተጠቅመው ደስታቸውን፣ሀዘናቸው ወይም ስሜታቸው ይገለፃሉ፡፡ ቀለማት እንደየማህበረሰቡ የተለያየ አመለካከት አና ትርጉም አላቸው፡፡

**መልመጃ 3.2**

1. የለበሳችሁት የልብስ ቀለም ምን እነደሆነ ለአስተማሪያቹ ግለፁ?
2. የምትወዱት የቀለም ዓይነት ምነድነው?
3. አከባቢያቹ ላይ በብዛት ምን ምን ዓይነት ቀለሞች ተመለከታቹ?

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- ስዕሎች(ፎቶግራፎች)
- ባንዴራ(ሰንደቅ አላማ)
- ሞዴል ክፍሎች
- ቀለም

**የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች**

- ምልከታ
- የግል ገለፃ
- የቡድን ገለፃ
- ግላዊ ማህደር
- የቃል ጥያቄ

**ጠቃሚ መረጃ**

- በዚህ ርዕስ ላይ መምህር ተማሪዎችን የተለያዩ ማህበረሰባዊ ዓውድ ላይ ያተኮሩ ፎቶግራፎችን ፤መመልከትና መለየት ላይ ያተኮረ ማህበረሰባዊ የቀለም ምልከታዎች መገንዘብ አለባቸው፡፡
- በዚህ የእድሜና የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ማሳተፍ ስለሚያስፈልግ አከባቢያቸው ላይ የሚገኙ ቀለሞች እነዲገለፁ በመጠየቅ እንዲለዩ እና ተፈጥሮን እነዲያደንቁ ለማድረግና እርሰ በእርስ እነዲማማሩ እድሉ ማመቻቸት የመምህራንና ወላጆች ሃላፊነት ነው፡፡

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- ስለዚህ መምህር በዚህ ርዕስ በማህበረሰብ ውስጥ ያለው የቀለማት ትር ጉም ከባህላዊ ምልከታዎች አካያ ለተማሪዎች መግለፅ እና ማሳየት፡፡
- ከባህላዊ እሴቶች መካከል አንዱን በመዉሰድ በስዕል እንዲገልጹ መጠየቅ፡፡
- የክልላቸው የሀገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚገኙ የቀለሞቹን ስም እና የሚወክሉትን ትርጉም ማሳየት እና መግለፅ፡፡
- የተለያዩ የቀለም መደቦች የሚያሳዩ ምሰሎች በማሳየት እና በመግለፅ የቤተሰቦቻቸው፣የጓደኞቻቸው እና የራሳቸው የልብስ ቀለም እነዲለዩ ማድረግ፡፡
- በተማሪ መፅሀፍ ላይ ለምሳሌነት የቀረቡት ሁለት ገፀ-ባህርያት(አበባ እና አበበ) የልብስ ቀለም ዓይነት ማሳየት እና መግለፅ፡፡




ምስል 3.8፡ የኢትዬጵያ ሰንደቅ ዓላማ

- **አረንጓዴ:** ለም መሬት እና እድገት
- **ቢጫ:** ብሩህተስፋ፣ፍቅር እና ሰላም
- **ቀይ:** የአባቶቻችን ደም፣ነፃነት እና እኩልነት

**የቀለም አይነቶች**

ቀለሞች በአይናችን በማየት እንለያቸዋለን፡፡ቀለም ለማየት ብርሃን ያስፈልገናል፡፡ብዙ የቀለም አይነቶች አሉ እነዚህም ቀይ፣ሰመያዊ፣ቢጫ፣አረንጓዴ፣ብርተትካናማ፣ወይንጠጅ፣ሃምራዊወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡




ምስል 3.9፡ የተለያዩ የቀለም አይነቶች




**የልብስ ቀለም መለየት**

| | |
|---|---|
| ቀይ  | ሰማያዊ  |
| ብርቱካንማ  | ቢጫ  |

ምስል 3.10፡ አበባ እና አበበ የተለያዩ የልብስ ቀለሞች ለብሰው

**መልመጃ 3.3**

1. አቮካዶ ምን አይነት ቀለም አለው?
2. ሰማይ ምን አይነት ቀለም አለው?
3. አበባ እና አበበ ምን አይነት ቀለም ለበሱ?
4. የቀለም አይነቶች ዘርዝሩ?
5. ብርቱካን ምን አይነት ቀለም አለው?
6. ሙዝ ምን አይነት ቀለም አለው?
7. አፕል ምን አይነት ቀለም አለው?

**መልመጃ 3.3፡ መልስ**

1. አረንጓዴ
2. ሰማያዊ
3. ቀይ፣ሰመያዊ፣ብርቱካናማ እና ቢጫ
4. ቢጫ፣ቀይ፣ሰመያዊ፣አረንጓዴ፣ብርቱካንማ፣ወይንጠጅ ፣ሀምራዊ ወ.ዘ.ተ.
5. ብርቱካንማ
6. ቢጫ
7. ቀይ

**ባህላዊ የቀለም ኣዘገጃጀት**

ተማሪዎች ኣከባቢያቸው ላይ ከሚገኙ ቁሳቁሶች እና ተፈጥራዊ ግብአቶች በመጠቀም የተለያዩ ቀለሞች ማዘጋጀት እነዲችሉ መምህር ከታች በቀረበው ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ እንዴት እነደሚዘጋጅ አሳይዋቸው፡፡

**1. አረንጔዴ ቀለም አዘገጃጀት**

| የቀለም ዓይነት | የሚየስፈልጉ ግብአቶች |
| --- | --- |
| አረንጓዴ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• ጎድጓዳ ሳህን<br>• የሻይ ብርጭቆ<br>• ብልቃጥ |

አረንጌዴ ቀለም ከተለያዩ አረንጋዴነት ከላቸው ቅጠላቅጠሎች ማዘጋጀት እንችላለን፡፡

**አሰራር**

1. መጀመርያ ያዘጋጀነውን የብሳና ቅጠል እንወቅጠዋለን፡፡
2. የተወቀጠውን ቅጠል በሳህን ውስጥ አድርገን በትንሹ ውሃ በመጨመር እንፈጨዋለን፡፡
3. የውሃውን መጠን በአንድ ተኩል የሻይ ብርጭቆ በማድረግ የተወቀጠ ቅጠል ላይ ሩብ(1/4) ብርጭቆ ውሃ በመጨመር እናማስለዋለን፡፡
   በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀው ቀለም ስዕል ልንስልበት እና በመቃ እያጣቀስን ልንፅፍበት እንችላለን፡፡

**2. ቢጫ ቀለም አዘገጃጀት**

| የቀለም ዓይነት | የሚየስፈልጉ ግብአቶች |
| --- | --- |
| ቢጫ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• አድ ጎድጓዳ ሳህን<br>• ቢላዋ<br>• የመቅመቆ ስር |

**አሰራር**

1. የመቅመቆ ስሩን በደንብ ማጠብ
2. ካጠብነው በኃላ የላይኛው የመቅመቆ ሽፋኑን በቢላዋ እንልጠዋለን፡፡
3. ከላጥነው በኃላ አድቅቀን በመክተፍ ፀሃይ ላይ እናደርቀዋለን፡፡
4. በፀሃይ የደረቀው የመቅመቆ ስር እንወቅጠዋለን፡፡
5. ድስት ለይ ውሃ በመጣድ ሲንተከተክ የተፈጨውን መቅመቆ ስር ድስት ለይ  በመጨመር እንዳይጓጉል በደንብ እናማስለዋለን፡፡
6. ከተጣደበት አውርደን ከቀዘቀዘ በኃላ ቀለል ያሉ ስዕሎች መሳል እና ማቅለም እንችላለን፡፡

**3. ቀይ ቀለም አዘገጃጀት**

| የቀለም ዓይነት | የሚየስፈልጉ ግብአቶች |
|---|---|
| ቀይ ቀለም | • ሙቀጫ (መፍጫ)<br>• ጎድጓዳ ሳህን<br>• ስካር(ሙጫ)<br>• ቀይ አፈር |

**አሰራር**

1. አከባቢያችን ላይ ቀይ አፈር በመፈለግ እናዘጋጃለን፡፡
2. ቀይ አፈሩን አስኪልም እንወቅጠዋለን፡፡
3. የተፈጨውን ቀይ አፈር በፈላ ውሃ በመጨመር እናማስለዋለን፡፡
4. ስካር  በመበጥበጥ ከሚፈላው ቀይ አፈር ጋር በደንብ ማማሰል፡፡

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- የክልላቸው የሀገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚገኙ የቀለሞቹ ስም  እና የሚወክሉትን ትርጉም በትክክል ማወቃቸው በጥያቄ ማረጋገጥ፡፡

- መሰረታዊ የቀለም መደቦች የሚያሳዩ ምስሎች በማሳየት ስማቸው እነዲገልፁ ማድረግ፡፡

- የቤተሰቦቻቸው፣የጋደኞቻቸው እና የራሳቸው የልብስ ቀለም ምን እነደሆነ መጠየቅ፡፡
- ተማሪዎች የተለያየ ወንዞች ፎቶግራፎችን በማሳየት ከተመለከቷቸው ፎቶዎች መካከል ቢያንስ 2 የሚሆኑ ፎቶዎችን መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፡፡

### 3.3.3. ትወና ከባህላዊ ምልከታ አኳያ

ትወና የዕለት ተዕለት ኑሮን ለመድረክ በሚመጥን መልኩ ከሽኖ በመድረክ ማቅረብ ነው፡፡ ትወና በገፀ-ባህሪያት ተከፋፍለው የሚተገበሩትን ታሪኮች ተግባራት ማሳያ ወይም መናገርያ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተለያዩ ባህሎችን ሀገረሰባዊ ድርጊቶችን በትወና ማቅረብ ማሳየት መናገር ይቻላል፡፡

ባህላዊ (ሀገረሰባዊ) ድርጊቶች ከትወና ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይህን ስንል ባህላዊ(ሀገርሰባዊ) ድርጊቶች በአንድ አከባቢ የሚገኝ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አምነው ተቀብለው የሚያከናውኑት ድርጊቶች፣እምነቶች ጊዜውን እና ቦታውን በመጠበቅ በየጊዜው የሚከናወኑ ድርጊቶች ናቸው፡፡ አንድ ትውልድ ለቀጣዩ ትውልድ ያስቀጥላል ቀደምት አባት አያቶቹ እንደከወኑት እሱም ይከውናል፡፡ ድርጊቶችም ሙሉ በሙሉ በማስመሰል ይከውናሉ፡፡ ከማስመሰል በላይ በመሆን ንግግሮችንም በተመሳሳይ እንደቀደምቶቹ እየደጋገሙ ይከውናሉ፡፡ ይህም ማስመሰል ወይም መተወን ነው፡፡

**መልመጃ 3.4**

1. ተማሪዎች በቡድን በመሆን ወንዶች ሆያሆዬ ሴቶች ደግሞ አበባ አየሽ በማለት ከውኑ፡፡

**ማጠቃለያ**

- ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ ስዕል፣ ቴያትር እና  ፎቶግራፍ የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባት ዘርፎች ሲሆኑ ለልጆች ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ላቸው የኪነ ጥበብ ዘርፎች ናቸው፡፡
- አድናቆት ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እውቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነው፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ጨዋታዎችን የምጫወቱት በማስመሰል የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን  በመጠቀም ስለሆነ በእነዚህ ጨዋታዎች ሳይረዱት ሳያውቁት የተለያዩ ገፅ-ባህርያትን በመውሰደ ይተውናሉ፡፡
- ሙዚቃ ለሰው ልጆች ሁሉ ከሀዘን መውጫ፣በደስታ ጊዜ መዝናኛ፣ተማሪዎች እያጠኑ እንደ መዝናኛ፣ ሥራዎችን በምንሰራበት ጊዜ እንደ መዝናኛ እና ወዘተ ተግባራትን ለመፈፀም የሚንጠቀምበት መሣሪያ ነው፡፡

**ማጠቃለያ መልመጃ**

1. በአከባቢያችሁ በሃዘን ጊዜ የምጠቀሙት የሙዚቃ መሣሪያ ግለፅ፡፡
2. የኢትዪጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ያሉት ቀለማት ትርጉማቸው ለመምህራቹ ግለፁ፡፡

**መልስ**

1. የዚህ ጥያቄ መልሶች በመምህሩ
2. **አረንጋዴ**፡ ለም መሬት እና እድገት

   **ቢጫ**፡ ብሩህተስፋ፣ፍቅር

   **ቀይ**፡ የኣባቶቻችን ደም፣ነፃነት እና እኩልነት

| ምዕራፍ 4 | አድናቂነት |
| --- | --- |

| ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 25 |
| --- | --- |

**መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ እይታዊና ክውናዊ ጥበባት በመጠቀም አድናቆትን /ማድነቅን/ መግለፅ ሲሆን በዚህ መሰረት ተማሪዎች ሙዚቃን፣ ስዕልን፣ ውዝዋዜንና ትወናን /ድራማን/ የማድነቅ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-**

- ❖ እይታዊና ከዉናዊ ጥበባትን ምንነት ያዉቃሉ
- ❖ እይታዊና ክዉናዊ ጥበባትን በተግባር ሰርተው ያሳያሉ
- ❖ የትውን እና የእይታ ጥበቦችን ተጠቅመው ተፈጥሮን ያደንቃሉ

## 4.1 የትውን እና የእይታ ጥበብ ክንዋኔዎች

| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 27 |
| --- | --- |

**መግብያ**

በዚህ በምዕራፍ የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ተማሪዎች ሙዚቃን፣ ስዕልን፣ ውዝዋዜንና ትወናን /ድራማን/ የማድነቅ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ምዕራፍ ነው፡፡

**ከረዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

| **ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**<br>➢ የተለያዩ መዝሙሮችን ይሰራሉ (ይዘምራሉ)<br>➢ ቀለል ያሉ ትወናዎችን ያከናውናሉ<br>➢ ቀለል ያሉ ውዝዋዜዎችን ይወዛወዛሉ<br>➢ የስዕልን ጠቀሜታ ይናገራሉ<br>➢ _ተፈጥሮን በስዕል ያደንቃሉ<br>➢ አከባቢያቸው ላይ የሚገኙ የስነ-ጥበብ ውጤቶች ያደንቃሉ |
|---|

### 4.1.1. በሙዚቃ ማድነቅ

በዚህ ክፍል ትምህርት ተማሪዎች የሚያከናውኑት ብዙ ክንዋኔዎች አሉ ማለትም ትውን ብቻውን ስንመለከት ሙዚቃና ትወናን ይይዛል በሙዚቃ እንዴት መተወን እንደሚችሉ በተገቢው ለተማሪዎች ግንዛቤን ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች የተለያዩሙዚቃዎችን ዕፈው እንዲያመጡና በዚያ ሙዚቃ እንድትውኑ በማድረግ በተጨማሪ ደግሞ ስለ እይታ ጥበብ ተገቢውን እውቀት ካስጨበጥን በኃላ እነዚህን ሦስቱን በአንድነት እንድያከናውኑ ማድረግ እና ለተማሪዎች በሚያስፈልጓቸው ነገር ሁሉ እርዳታ በማድረግ እነዚህን እውቀቶች ማስጨበጥ የግድ ይለናል፡፡

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)**

- የትውን እና የእይታ ጥበብ ከማህበረዊ ክንዋኔዎች አንፃር ምን እንደምመስሉ አብራሩ፡፡

## የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

- የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ
- በግል እና በቡደን የተግባር ሥራ እንዲሰሩ ማድረግ
- ቀለል ያሉ መዝሙሮችን በውዝዋዜ እንድሰሩ ማድረግ
- ስለ ሠሩት ሥራ ገለጻ እንድያደርጉ ዕድል መስጠት
- የሠሩትን ሥራ ከሌሎች ቡድኖች ጋር ማወዳደር

## የመማር ማስተማር ግባዓቶች

- በተለያዩ ቦታዎች የተሰሩ ውዝዋዜዎቸን እንዲያዩ ማድረግ
- የተቀዱ መዝሙሮች
- ምቹ ለልጆች ለመጫወት የሚሆን የመጫወቻ ቦታዎ

## ክትትል እና ግምገማ

- ስለ ሙዚቃ እና ስለ ውዝዋዜ ያላቸውን ዕውቀት በቀላል ጥያቄ ማረጋገጥ፡፡
- ውዝዋዜውን ሲሰሩ በትክክል እየተወዛወዙ መሆናቸውን በመከታተል ማረጋገጥ
- እነዚህን መዝሙሮችና ውዝዋዜ በደስታ እየሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ውዝዋዜ በሚስበት ሰዓት ምቹ ቦታ ላይ መቆማቸውን ማጋገጥ እና ወ.ዘ.ተ.......

## ጠቃሚ መረጃ

ሙዚቃ ለሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ተግባር መገለጫ ለስራው ቅልጥፍና ተግባር መሣሪያ እንደሆነ ማሳወቅ ይልቁኑ ደግሞ ለሕፃናት ሁሉ ነገራቸው እንደሆነ እውቀትን ማስጨበጥ ይኖርብናል፡ ሁሉ ነገራቸው ስንል ሕፃናት በሙዚቃ የተነገራቸውን እውቀት በየትኛውም ጊዜ የማስታውስ አቅምና መቼም እነደማይረሱና በጨዋታና በውዝዋዜ ሊገልፁ እንደሚችሉ እንመለከታለን፡፡

ስለዚህ ሙዚቃ ለልጆች ዕውቀት አስፈላጊ መሣሪያ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህ ዘመን በተሻሻሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች በመታገዝ ልጆችን ለተሸለ ዕውቀት እና ባህላቸውን የሚያከብሩ እንድሆኑ ከመምህራን ጎን ማህበረሰቡና ወላጆች ሊቆሙ ይገባቸዋል፡፡

## ጨረቃ ድንቡለቃ




ጨረቃ ድንቡለቃ
አዬ ቤት ገባች አውቃ
አዬ ቤት ያሉ ሰዎች
ፈተጉ ፈታተጉ
በቁሪፍቱ አስቀመጡ
ቁሪፍቷ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጡ
አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ያችን ትተሽ ይህችን ቶሎ


## ጨረቃ ድንቡለቃ



ጨ ረ ቃ ድ ቡ ሎቃ አ ፄ ቤት ገባቿ አዉ ቃ አ ፄ ቤት ያ ሉ ሰ ዎ ቿ ፈ ተ ጉ ፈ ታ ተጉ



በ ቁ ሪ ፍ ት አ ስቀ መጡ ቁ ሪ ፍ ቷ ስት ሰበ ርበ ዋን ቸጬ ገለ በጡ አጃ ቆሎ ሰንዴ ቆሎ



ያቾ ንት ተ ሽ ይ ህ ቾን ቶ ሎ

## ኤሊ እና ጥንቸል



**ኤሊ እና ጥንቸል ተነጋገሩ**

**ማራቶን እሩጫ ሊወዳደሩ**

ውድድሩ ሲያበቃ ሩጫው
እስኪ ገምቱ የማን ነው ዋንጫው
እነ ጦጣና እነ ዝንጀሮ
እነ ተኩላ እና እነ ቀበሮ
ውድድር ልያዩ ተሰባስበዋል
ኤሊ እና ጥንቸል ተዘጋጅተዋል
ኤሊየ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ
ጥንቸልዋ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ
ሽጉጥ ሲቶከስ ጥንቸል በረረች
ኤሊ እንደ አቅሟ ተውተረተረች
ጥንቸል ፈጥና ከዓይን እርቃለች
ድንጋዩ ከብዷት ኤሊ ደክማለች
ጥንቸልዋ በርቺ በርቺ እንዳትረች (2)
ኤሊ ቀርፋፋ መቼም አትቀድመኝ
ትንሽ ልተኛ መቼም አትቀድመኝ
ትንሽ ልተኛ በጣም ደከመኝ
ብላ ብተኛ ስለናቀቻት
ቀረፈፍ እያለች ኤሊ አለፈቻት
ኤልዬ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ (2)
ኤሊ አሸንፋ ገመድ ስትበጥስ
ጥንቸል ነቃች ሕልሟን ሳትጨርስ
ጥንቸል አፈረች አንገቷዋን ደፋች
ባልናኳት ብላ በጣም ተከፋች
ኤልዬ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ (2)

**መልመጃ** 4.1

1. በአከባቢያችሁ የሚታወቁ ሙዚቃዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ እየዘመራችሁ አሰሙ፡፡
2. በአከባቢያችሁ አርሶ አደሮች (ገበሬዎች) በሥራ ቦታ የሚዘምሩትን ሁለት መዝሙሮችን ግለፁ፡፡

**መልመጃ** 4.2

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ**

1) ------------ ለሰው ልጆች ሁሉ ከሀዘን መውጫ፣በደስታ ጊዜ መዝናኛ ሊሆን ይችላል፡፡

   ሀ/ ሙዚቃ ለ/ የእይታ ጥበብ ሐ/ ተውኔት መ/ ሁሉም

2) ገበሬው በእርሻ ቦታ በሚለው ግጥም ስንት ስንኝ አለው

   ሀ/ 4 ለ/ 6 ሐ/ 5 መ/ 3

3) ኤሊና ጥንቸል በ----------- ሩጫ ተወዳደሩ

   ሀ/ ማራቶን ለ/ ውሃ ዋና ሐ/ ሀእናለ መ/መልስ የለም

4) እስኪ ገምቱ የማን ነው ዋንጫው ብሎ የተሰበሰቡት እነማን ናቸው?

   ሀ/ ጦጣ ለ/ ዝንጀሮ ሐ/ ተኩላ እና ቀበሮ መ/ ሁሉም

5) ሽጉጥ ሲቶኮስ ጥንቸል በረረች ኤሊ እንደ አቅሟ -----

ሀ/ በረረች ለ/ ደከመች ሐ/ ተውተረተረች መ/ሁሉም

**መልመጃ 4.1፡ መልስ**

መልመጃ 4.1 ተማሪዎች በተግበር ሲሳሩ ተመልክተዉ ይገምግሙ(መልሰ ይስጡበት)

**መልመጃ 4.2**

1. መ
2. ሰ
3. ሀ
4. መ
5. ሐ

**4.1.2. ስዕልን በመስራት ማድነቅ**

አድናቆት ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እውቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነው፡፡ አከባቢያችን ላይ ብዙ የሚደነቁ ነገሮች አሉ፡፡

**የማነቃቅያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ለስዕል ያላችሁን አድናቆት በየግላችሁ መምህራችሁ በመያሳዩት መሰረት ስዕል በመስራት አድናቆታችሁን ግለፁ፡፡

**ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች/መርጃ መሳሪያዎች/**

- እርሳስ፣ወረቀት፣ ላጲስ
- የተለያዩ ስዕሎች
- መለማመጃ ክፍል
- ልዩ ልዩ ባህላዊ ዉዝዋዜን የሚያሣዩ ስዕሎች

**የመማር ማስተማር ስነ ዘዴ**

- ምልከታ
- የግል ገለፃ
- የቡድን ገለፃ
- ግላዊ ማህደር
- የቃል ጥያቄ

**መሪ ተግባራት/ማነቃቂያ**

**ጠቃሚ መረጃ**

- መምህር የተለያዩ ምስሎች በምዘጋጀት ተማሪዎች እንደየ አካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚያዉቋቸውን ተፈጥራዊ ነገሮች(ተራሮች፣ወንዞች፣ሰማይ፣ዳመና፣አበቦች፣ወፎች፣የቤት እና የዱር እንስሶች)የመሳሰሉት በተንቀሳቃሽ ምስል ያሳይዋቸው፡፡
- ካዩት ምስሎች ዉስጥ ለተማሪዎች የተመቻቸውን እንዲመርጡና በደብተራቸው እየሳሉ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- ርዕሱን በሰሌዳ በመጻፍ ማስተዋወቅ እና ምሳሌ በመስተት ማስረዳት፡፡
- ግልጽ እና በቀላሉ የሚውቋቸውን የሚያዉቋቸውን ተፈጥራዊ ነገሮች(ተራሮች፣ወንዞች፣ሰማይ፣ዳመና፣ አበቦች፣ወፎች፣የቤት እና የዱር እንስሶች)ተማሪዎች እንዲናገሩ እድል መስጠት፡፡
- ከተማሪዎች መልስ በመነሳት ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት ማስረዳት
- ሲጽፉ የፊደል ግድፈት እንዳይኖር ዕየዞሩ መመልከት እና እርማት መስጠት፡፡
- ተፈጥሮን እንዲያደንቁ ምስሎች ማሳየት

- ካዩት ምስሎች ዉስጥ ለተማሪዎች የተመቻቸውን እንዲመርጡና በደብተራቸው እየሳሉ እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- ተማሪዎች የሚያዉቋቸውን ተፈጥራዊ ነገሮች መካከል ቢያንስ ሁለት እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ፡፡
- ስዕሉን ሲሰሩት የተሰማቸውን ስሜት በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፡፡
- ጥሩ የሰራ ተማሪ ሲኖር ለሌሎች እነዲያሳይ በማድረግ ማበረታታት፡፡

**መልመጃ 4.3**


1.ላይ በተቀመጠው ምሳሌ መሰረት አበባ ሰላችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### 4.1.3 ትወናን /ድራማን/ ትወና በመስራት ማድነቅ

ተማሪዎች የተለያዩ ጨዋታዎችን የምጫወቱት በማስመሰል የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን ድርጊያዎችን በመጠቀም ስለሆነ በእነዚህ ጨዋታዎች ሳይረዱት ሳያውቁት የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን በመውሰደ ይተውናሉ፡፡

ለምሳሌ፡ ዕቃ ዕቃ ስጫወቱ የአባትን የእናትን የልጅን ወዘተ ገፀ-ባህርያት በመውሰድ በቤታቸው ውስጥ ቤተሰቦቻቸው ሲከውኑ ያዩትን የሰሙትን ያስመስላሉ፡፡ እንደ ሆያ ሆዬ፣አበባየሽ ሆይ የመሳሰሉ ጨዋታዎችን ደግሞ ግጥም ዜማ እና ድራማዊ ድሪጊታቸውን ጨምሮ የሚከውኑበት ስለሆነ ልጆች በጨዋታ በማስመሰል እና በመተወን ከዚሁ ድርጊት እየተለማመዱ ያጠናሉ ያቀርባሉ፡፡

## ሀገሬን ያያችሁ



አጫዋች ፡- ሀገሬን ያያችሁ

ተቀባይ፡- አላየንም ባካችሁ

አጫዋች፡- ሀገሬን ያችሁ

ተቀባይ፡- አላየንም ባካችሁ

አጫዋች፡- ይች የማን ሀገር ናት

ተቀባይ፡- የኔ ሀገር የኔ እናት

**መልመጃ 4.4**

1. ከመጽሐፉ ላይ ያለውን ሀገሬን ያያችሁ የሚለውን ጨዋታ ግጥም ልመዱ፡፡
2. በጨዋታ ቦታ ክብ ሰርታችሁ ተቀመጡ፡፡
3. የለመዱትን ግጥም በማህረቤን ያያችሁዜማ ሀገሬን ያያችሁ ብላችሁ ተጫወቱ፡፡

**ማጠቃለያ**

- ሙዚቃ፣ውዝዋዜ፣ ስዕል፣ ቲያትር እና ፎቶግራፍ የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባት ዘርፎች ሲሆኑ ለልጆች ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና አካላዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የኪነ ጥበብ ዘርፎች ናቸው፡፡
- አድናቆት ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እውቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነው፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ጨዋታዎችን የምጫወቱት በማስመሰል የተለያዩ ገፀ-ባህርያትን ድርጊያዎችን በመጠቀም ስለሆነ በእነዚህ ጨዋታዎች ሳይረዱት ሳያውቁት የተለያዩ ገፅ-ባህርያትን በመውሰድ ይተውናሉ፡፡
- ሙዚቃ ለሰው ልጆች ሁሉ ከሃዘን መውጫ፣በደስታ ጊዜ መዝናኛ፣ተማሪዎች እያጠኑ እንደ መዝናኛ፣ ሥራዎችን በምንሰራበት ጊዜ እንደ መዝናኛ እና ወዘተ ተግባራትን ለመፈፀም የሚንጠቀምበት መሣሪያ ነው፡፡

**የማጠቃለያ መልመጃ**

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታውቁትን የውዝዋዜ አይነት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ መጫወት አሳዩ፡፡

2. ልጆች በአካባቢያችሁ የምታገኙትን አበባ ንድፍ በየግላችሁ በንድፍና ቀለም በመቀባት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

3.ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታዉቋቸውን የሰዎች ወይም የእንስሳት ድምጽና እንቅስቃሴን አስመስላችሁ በመተወን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡

4. ተፈጥሮን እንዴት ማድነቅ እንችላለን

1. ሽጉጥ ሲተኮስ ጥንቸል በረረች ኤሊ እንደ አቅሟ ______

ሀ. በረረች ለ. ደከመች ሐ. ተውተረተረች መ. ሁሉም

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክልለኛዉን መልስ ምረጡ

1. __________ለልጆች የማህበረዊ፤ ስነ-ልቦናዊና አካለዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ የላቸዉ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች ናቸዉ

ሀ . ሙዚቃ ለ. ዉዝዋዜ ሐ. ሀ እና ለ

2. __________ማለት ለአንድ ስራ ወይም ተፈጥራዊ ለሆኑ ነገሮች እዉቅና ወይም ምላሽ መስጠት ማለት ነዉ

ሀ. ቲያትር ለ. አድናቆት ሐ. ጨዋታ

| ምዕራፍ 5 | ግንኙነት |
|---|---|

| ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 20 |
|---|---|

**መግቢያ**

እይታዊና ክውናዊ ጥበባት በአንድም በሌላ መልኩ የራሳቸው የሆነ የእርስ በርስ ዝምድና ያላቸው ሲሆኑ እይታዊ ጥበባት የምንላቸው ሲከወኑ(ሲተገበሩ) በአይን የሚታዩ እንደ ስዕል ፣ቅርጻ ቅርጽ ፎቶግራፍ ወዘተ የመሳሰሉት ሲሆኑ ክዉናዊ ጥበባት የምንላቸው ደግሞ ሲከወኑ( ሲተገበሩ) በአይን የሚታዩ ወይም በጆሮ የሚደመጡ እንደ ሙዚቃ፣ቴያትር( ድራማ)፣ ዉዝዋዜ፣ፊልም፣ትወና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለ እያንዳንዳቸው የእርስ በርስ ዝምድና እንዲሁም ሌሎች ትምህርቶችን ለማስተማር ያላቸውን ሚና እንመለከታለን፡፡

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡**

1. የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባት ዝምድናን ይረዳሉ
2. የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባትን ዝምድና ያደንቃሉ
3. የእይታዊና ክዉናዊ ጥበባትን በተግባር ስርታችሁ ያሳያሉ

## የቅድመ እዉቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች የምታውቋቸውን ሙዚቃዎች በመጫወት ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ አሰሙ

2. ተማሪዎች የሙዚቃ፣ የስዕል፣ የውዝዋዜና ትወና /ድራማን/ ዝምድናን እንዴት ይገለፃል

3. ተማሪዎች የስዕል ትምህርት ሌሎች ትምህርቶችን ለመማር ያለው አስፈላጊነት ምንድን ነው

## 5.1 በሰውነት አካላት የሚሰሩ ሙዚቃዎች

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 5 |

**መግቢያ**

በሰው አካል የሚሰሩ ሙዚቃዎች በሁሉ ማህበረሰብ፡ መካከል ልተገበሩ ይችላሉ፡፡ ይህንን ሲንል በየኃይማኖት ቦታዎች፣በሃዘንና በደስታ መግለጫዎች ፣ በሥራ ቦታ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፤

በሰው አካል የሚተገበሩ ስንል እጅን በማጨብጨብ ፣ የእግር እንቅስቃሴ በማድረግ እና የሙዚቃ መሣሪያዎችን ሳይጠቀሙ ሕፃናት የሚተገብሩ ተግባራት ናቸው፡፡

በሁሉም ማህበረሰብ ልጆች የሙዚቃ ምት(ስልተምት) ጠብቆ መጫወት እና ጠወደፊት ትምህርታቸውን የሚያጠናክሩበት ዘዴ ነው፡፡

ስለዚህ በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ልጆች (ህጻናት) የራሳቸውን የሰውነት አካላቸውን በመጠቀም የሙዚቃ ምት(ስልተምተ) ጠብቀው እንዲጫወቱበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

| **ተማሪዎች ይህን ረዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ**<br>➢ የሰውነት አካላትን በመጠቀም የተለያዩ ሙዚቃዎችን ይጫወታሉ<br>➢ በሰውነት አካላት የሚፈጠሩ ድምፆችን ይገልፃሉ<br>➢ የሰውነት አካላችን በመጠቀም ሪቲምን (ስልተ ምት)ይቆጥራሉ<br>➢ የሙዚቃ መሣሪያ ሳይነኖር ሪቲም (ስልተምት) ጠብቀው እንዴት እንደሚጫወቱ ይገልጻሉ<br>➢ ልጆች የራሳቸውን የሰውንት አካላት ተጠቅመው የሚጫወቱትን የተለያየ ጨዋታዎችን ያሳያሉ። |
|---|

**ማነቃቂያ (መሪ ተግባራት)አንድ**

➢ ልጆች የሙዚቃ መሣሪያ ሳይኖር በስውነት አካላቸውን በመጠቀም ሙዚቃን እንድሳሩ አበረታቱ።

**የመማር ማስተማር ሥነ- ዘዴዎች**

➢ ገለፃ
➢ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ
➢ የሰውነትን አካላት በማስነካት(በተግባር ሥራ)
➢ ጥያቄ በመጠየቅ (ጥያቄ እና መልስ)
➢ በማወያየት

**የመማር ማስተማር ግባዓቶች**

➢ በክፍላቸው የሚገኙ ጠረጴዛዎችን በመምታት
➢ የተቀረፁ ድምፆችን በካሴት፣በቴፕ ሪከርደር በማስማት
➢ የትወና መሣሪያዎችን በማሳየት እና ተጠቅሞ ድምፅ በማሰማት
➢ ናሙናዎችን በመጠቀም

**ጠቃሚ መረጃ**

- የትምህርት አቀባበል ሁኔታን በመለየት የሰውነትን አካል ማንቀሳቀስ የአዕምሮ የትምህርት አቀባበል ሁኔታን ያዳብራል፡፡
- የተማሪዎች የአቀባበልና የፈጠራ ሥራን እንድያዳብሩ የሰውነት እንቅስቃሴን እንዲያደርጉ ማደረግ ያስፈልጋል፡፡


**ክትትል እና ግምገማ**

- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት
- የሰውነት አካለትተጠቅሞ ሪትም (ስልተምት) ጠብቆ እንዲጫወቱ የክፍል ሥራ መስጠት
- የቤት ሥራ መስጠት
- በየቀኑ የተለያዩ ምዘናዎችን በመስጠት
- ግብረ መልስ ከተማሪዎች በየጊዜ በመቀበል



ምስል 5.1፡ የተለያዩ የጭብጨባ አይነቶች

## ጨረቃ ዱንቡለቃ



ጨረቃ ዱንቡለቃ
አፄ ቤት ገባች አውቃ
አፄ ቤት ያሉ ሰዎች
ፈተጉ ፈታተጉ
በቁሪፍት አስቀመጡ
ቁሪፍቷ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጡ
አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ያችን ትተሽ ይችህን ቶሎ

**መልመጀ 5.1**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ከሚከተሉት ውስጥ ድምፅ ሊሰጠን የሚችል የሰውነት የሙዚቃ ሪቲም (ስልተምት)

   ሀ/በመርገጥ ለ/ በማጨብጨብ ሐ/ጣቶችን ጠቅ ጠቅ በማድረግ መ/ ሁሉም መልስ ናቸው

2. ብዙ ሰዎች በሕልም ውስጥ -------- ይሰማሉ፡፡

ሀ/ ሙዚቃን ለ/ ኳስ ጨዋታን ሐ/ ይሮጣሉ

መ/ ለ እና ሐ

3. አንዳንድ ሰዎች --------- ሲሰሙ ቀለሞችን ያያሉ፡፡

ሀ/ ጩሀት ለ/ሙዚቃን ሐ/ ድርሰትን መ/ መልስ የለም

**መልመጃ 5.1፡ መልስ**

1. መ
2. ሀ
3. ለ

## 5.2. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነት

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 5 |

**መግቢያ**

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነታቸውን በዚህ ምዕራፍ በደንብ አድርገን እናያቸዋለን፡፡

**ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ

- የተለያዩ የኪነ ጥበብ ጨዋታዎች በመጫወት ያሳያሉ
- ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ የተለመዱ አካላትን መርሆችን በመጠቀም ያሳያሉ (ይገልፃሉ)
- የሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ የፈጠራ ችሎታ ያደብራሉ
- የሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግኙነትን በደንብ ያውቃሉ

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ግንኙነት እና ልዩነት እንዲገልፁ ያበራታቱ፡፡

**የሚያስፈልጉ ግብዓቶች**

- የሙዚቃ መሣሪያዎች
- ስዕላዊ መግለጫዎች

**ጠቃሚ መረጃ**

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ ተዛማች እና አንዱከአንዱ የማይነጣጠል የትምህርት ዘረፍ ነው፡፡ ሁለቱም ዘርፎች ሰዎች አዕምሮቻቸውን በመጠቀም የሰውን ስሜት የሚያነቃቁ ነገሮችን ለመፍጥር ይችላሉ፡፡

ሙዚቃ ዜማን፣ስልተምት(ሪትም)፣ሃርመኒ(ህብረ ዜማ) በመጠቀም የሰውን ስሜትን በማነቃቃት እንዱሁም ሰዎች በአካላቸው እንድንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስበርሰ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው፡፡ አንደ ኪነ ጥበብ ቅርፅ እንከን የለሽ ወደ ሌለ ይለወጣል ሙዚቃ ከጥንት ጀምሮ ለብዙ ሰዓሊዎች እና የእይታ አርቲስቶች ማነቃቂያ እና መነሻ ነው፡፡ ለብዙኃን እንደ መዝናኛ እና ንቁ የጥበብ ተሳትፎ የሙዚቃ ተወዳጅነት በዓለም ውስጥ በሚሊዮኖች በምቆጠር የሙዚቃ ቡዱኖች አማካኝነት ይታያል፡፡ እኛ በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙዚቃ ነው ለማለት እንችላለን፡፡

ብዙ ሰዎች በሕልም ውስጥ ሙዚቃን ይሰማሉ እና አንዳንዶች ሙዚቃን ሲሰሙ ቀለሞችን ያያሉ፡፡

ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ የተለመዱ አካላትን መርሆችን እና ሂደቶችን ያረጋሉ ፡፡

| የሙዚቃ አለበዊያን | የእይታ ጥበብ አለባዊያን እና መሪህ |
|---|---|
| ሜሎዲ(ዜማ) | ሙቭመንት (እንቅስቃሴ) |
| ሪትም (ስልተምት) | ሪትም(ድግግሞሽ) |
| ቴክስቸር ( የድምጽ መነባበር) | ቴክስቸር(ልስላሴ እና ሸካራነት) |
| ፎርም(አዝማችና ቁጥርን የምንለይበት) | ፎርም(ቅርፅ) |
| ቲምበር (የድምፅ ቃና) | ከለር(ቀለም) |
| ሀርሞኒ (የሙዚቃ ውበት) | ሀርሞኒ(ውበት) |

## የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች

- ተማሪዎች ከአከባቢያቸው የሰውነትን ሙዚቃ እንዲዘምሩ ዕድል መስጠት
- ተማሪዎች የራሳቸውን የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም ንቁ ተሳትፎ በክፍላቸው እንዲያደርጉ ማበረታታት፡፡ ከዚያ በየስልፉ ሜዳ ላይ ለተማሪዎች ሙዚቃ እንድዘምሩ ማድረግና በተለያዩ የክበብ ተሳትፎ እንዲያደረጉ መግለፅ ያስፈልጋል፡፡

## ክትትልና ግምገማ

- በየክፍለ ጊዜ አቴንዳንስ በመውሰድ
- ጥሩ ተሳትፎ ላደረጉ ተማሪዎች ሽልማትን በመስጠት
- በየጊዜ ለተማሪዎች ምዘናን (ፈተና)መስጠት
- ከተለያዩ ሙዚቃ የሰሙትን የክፍል ተማሪዎች እንድገልፁ ለሁሉም ተማሪዎች ለሴቶችና ለወንዶች እኩል የሆነ ተሳትፎን መስጠት፡፡

**መልመጃ 5.2**

**ሀ.የሚከተሉትን ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1. ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስ በእርስ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው፡፡
2. እኛ በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙዚቃ ነው ለማለት እንችላለን፡፡
3. የሰው አካል የየሙዚቃ መሣሪያ ልሆን አይችልም፡፡
4. በሙዚቃ እና በእይታ ጥበቦች መካከል ብዙ የጋራ ነገሮች አላቸው፡፡

**መልመጃ 5.2፡ መልስ**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት

## 5.3 የትወና እና የእይታ ጥበባት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለማገዝ ያለው ሚና

| | |
|---|---|
| ለርዕሱ የተመደበ ክፍለ ጊዜ ብዛት | 19 |

**መግብያ**

የትወና እና የእይታ ጥበብ የቋንቋ ትምህርትን በቀላሉ ለልጆች ለማስተማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ይህም ማለት የአማርኛም ይሁን የእንግሊዝኛን ፊደላት በቀላሉ አሳምረው ለመጻፍ ፊደላትን እንዴት መቅረጽ እንዳለባቸው ከስነ ጥበባት ትምህርት መካከል በስዕል ዘርፍ ይማራሉ፡፡

ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ግንኙነት በጣም የጠበቀ ነው፡፡

ሙዚቃ ማለት ሌሎችን የትምህርት ዓይነቶች በሚማሩበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ እያደረጉ አዕምሮአቸው የሚያድሱበት ተግባር ነው፡፡

ተማሪዎች ሙዚቃን ከሒሳብ ትምህርት ዓይነት ጋር መቀነስ፣መደመር፣ማባዛት እና ማካፈልን እና የሕሳብ ቁጥሮች በዜማ እንዲማሩ ይረዳል፡በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር የስሜት ህዋሳት እንድለዩ በሙዚቃ መልክ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

እንደዚሁም ከቋንቋ ትምህርት ዓይነቶች ጋር የፊደል ገበታዎች የፊደል ቅርፅን በሙዚቃ ቢማሩ ይመቅማል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሙዚቃን እያዛመዱ እንድማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ከርዕሱ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኃላ፡-**

- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ግንኙነት ይረዳሉ፡፡
- ስነ-ጥበብ በመጠቀም የጤና እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት፣የቋንቋ ትምህርት፣ሒሳብ ትምህርት፣አከባቢ ሳይንስ ትምህርት፣የማህበራዊ ሳይንስ እና ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማቀናጀት አጋዥ ንድፎችን ይሰራሉ፡፡

**ማነቃቅያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች የትወና እና የእይታ ጥበባት ለሌሎች የትምህርት አይነቶች ለማገዝ ያለው ሚና ገልፁ፡፡


**ጠቃሚ መረጃ**

ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ግንኙነት በጣም የጠበቀ ነው፡፡
ሙዚቃ ማለት ለሎችን የትምህርት ዓይነቶች በሚማሩበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ እንቅስቃሴና ውዝዋዜ እያደረጉ አዕምሮአቸው የሚያድሱበት ተግባር ነው፡፡
ተማሪዎች ሙዚቃን ከሒሳብ ትምህርት ዓይነት ጋር መቀነስ፣መደመር፣ማባዛት እና ማካፈልን እና የሕሳብ ቁጥሮች በዜማ እንዲማሩ ይረዳል፡በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ጋር የስሜት ህዋሳት እንድለዩ በሙዚቃ መልክ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

## 5.3.1 ሙዚቃ የአከባቢ ሳይንስ ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

**የስሜት ህዋሳት ስንት ናቸዉ**

አምስት ናቸዉ
አይን አለኝ አያለዉ
ጆሮ አለኝ እሰማለዉ
በአፍንጫዬም አሸታለሁ
በምላሴ እቀምሳለሁ
መዳሰሻም እጅ አለኝ
የስሜት ህዋሴን አወቁልኝ፡፡



ምስል 5.2፡ አምስቱ የስሜት ህዋሳት መዘመር

### 5.3.2 ሙዚቃ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያለው ጠቀሜታ

የቋንቋ ትምህርት ዓይነቶች ጋር የፊደል ገበታዎች የፊደል ቅርፅን በሙዚቃ ቢማሩ ይመቅማል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሙዚቃን እያዛመዱ እንድማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ፊደላትን ለማወቅ ይሄንን መዝሙር መጠቀም እንችላለን፡፡

እስኪ ልጆች ቸብ ቸብ በእጃችን በሀገራችን ፊደል እስኪ ሀ ሁ እንበል

ሀ ሁ ሂ ምግብ ስንበላ

ረ ሩ ሪ ሁላችንም በጋራ

ኘ ኙ ኚ ፍቅር እንዲደራ

መ ሙ ሚ ኢትዮጵያ ሀገሬ

ነ ኑ ኒ እስኪ ሳቂ ዛሬ

በ ቡ ቢ እኛ አለን ልጆችሽ

ደ ዱ ዲ  አምረን በምድርሽ

ዘ ዙ ዚ ዘላለም ኑሪልን

ቀ ቁ ቂ እኛንም አፍቅሪን

**ጠንቃቃ ተማሪ**



ጥንቃቄን  ያውቃል ጠንቃ ቃተማሪ

ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ

የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል

የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል፡፡

የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን

መኪና ይቆማል ጠብቆ ሕጉን

ወንዝ ስንሻገር ግራ ቀኝ አይተን

መጠንቀቅ አለብን ድልድይ ላይ ሆነን

ጥንቃቄ ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ

ሀሳቡን ሰብስቦ በመንገድ ተሻጋሪ

የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል

የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል፡፡

**ጠንቃቃ ተማሪ**




## ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ስዕሎች(ፎቶግራፎች)
- የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻዎች
- እርሳስ፣ባለቀለም ጠመኔ(ክራዮን) እና አከባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች
- ፎቶ ማንሻ (ካሜራ)
- ሞዴል ክፍሎች

## የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች

- ምልከታ
- የግል ገለፃ
- የቡድን ገለፃ
- ግላዊ ማህደር
- የቃል ጥያቄ

**ጠቃሚ መረጃ**

- መምህር ተማሪዎች በዚህ የክፍል ደረጃ ፎቶግራፎችን መመልከትና መለየት ላይ ያተኮረ ስለሆነ ይህ ርዕስ ለማስተማር ከላይ ለተቀመጡ ርዕሶች የሚወክሉ ፎቶዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።
- በዚህ የእድሜና የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በተለያዩ ስልቶች የተነሱ አከባቢያቸው እንዲለዩ እና ተፈጥሮን እነዲያደንቁ ለማድረግና ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ሲሸጋገሩ የራሳቸው ፈጠራ ተጠቅመው ፎቶግራፍ የማንሳት ፍላጎት ወይም ዝንባሌ፣ እውቀትና ክህሎት ማስጨበጥ የመምህራንና ወላጆች ሃላፊነት ነው።

**የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች**

- ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን እና የሚያገኟቸውን አከባቢያቸውን እንዲለዩ እና ተፈጥሮን እንዲያደንቁ ስዕሎች (ፎቶግራፎችን) በማሳየት እንዲናገሩ /እንዲዘረዝሩ/ እድል መስጠት።
- አከባብያዊ እና ተፈጥሮኣዊ ገጽታ የሚወከክሉ ፎቶዎች በማለት እንዲከፋፍሉ እንዲመድቡ ማድረግ እንደሁም ሌሎች ምሳሌዎች በማሳየት ማብራሪያ መስጠት።
- የእይታ ጥበብ በመጠቀም የተለያዩ የትምህርት አይነቶች ላይ ያላቸውን እውቀት ያዳብራሉ።
- የተለያየ ወንዞች ፎቶግራፎችን በማሳየት የመሰላቸውን እንዲናገሩ እድል መስጠት።

**የግምገማና ክትትል ስልቶች**

- ተማሪዎች የሚያዉቋቸውን ተፈጥራዊ ነገሮች መካከል ቢያንስ ሁለት እንዲናገሩ የቃል ጥያቄ መጠየቅ።
- ስዕሉን ሲሰሩት የተሰማቸውን ስሜት በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ።
- ከተሰሩት ተፈጥሮ የማድነቅ ሰዕሎች የተሻለ ሰዕል የሰራ ተማሪ በምልከታ ማረጋገጥ።

### 5.3.3 ስነ-ጥበብ  የጤና እና ሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

የጤና እና የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት ለልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህን ትምህርት የበለጠ ልጆች እንዲገነዘቡትና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ በእይታዊና ክወናዊ ጥበባት ማስተማር ትምህርቱን አይረሴ ከማድረጉም ባሻገር ልጆች መዝሙሮችን እየዘመሩ በነጻነት አካላዊ እንቅስቃሴን እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል ፡፡

በተጨማሪም ያዩትን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በንድፍ እንዲለማመዱ እና የስዕል ፍላጎታቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል፡፡ ልጆች የአካል እንቅስቃሴ እያደረጉ መዝሙሮችን በሚዘምሩበት ጊዜ የተስተካከለ የሰዉነት ቅርጽ እና የተስተካከለ የትንፈሳ ስርአትም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያዩትን ስፖርታዊ እንቅስቃሴ አስመስለው በመስራት የትወና ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡




ምስል 5.3፡ ቀላል ጨዋታዎች እና የአካል እንቅስቃሴ


### 5.3.4 ስነ-ጥበብ የሂሳብ ትምህርትን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

እይታዊና ክዉናዊ ጥበባት የሒሳብ ትምህርትን ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የቁሳቁሶች ንድፍ እና ይዘት፣ የሒሳብ ምልክቶች እና ቁጥሮችን በስእል እና በሙዚቃ በማስቀመጥ የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

### 5.3.5 ስነ-ጥበብ የቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸው

*ሀ. የአማርኛ ፊደላትን  የአፃፃፍ ስልት መለማመድ*





| | | |
|---|---|---|
| **ወ** | **ወንበር** |  |

ምስል 5.4፡ ስዕልን ተጠቅሞ ፊደላት እና ቃላት ማስተማር

## መልመጃ 5.3


1. ተማሪዎች የአማርኛ ፊደላትን ጥሩ በሆነ የአፃፃፍ ስልት በመፃፍ ቀለም ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ


በአማርኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት




ምስል 5.5 በአማርኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት


ለ. የእንግሊዝኛ ፊደላትን የአፃፃፍ ስልት መለማመድ




| | | |
|---|---|---|
| O | orange |  |
| F | Fish |  |

ምስል 5.6፡ ስዕልን ተጠቅሞ ፊደላት እና ቃላት ማስተማር

## በእንግሊዝኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት




ምስል 5.7፡ በእንግሊዝኛ ፊደላት የሰው ፊት የመሳል ስልት

**መልመጃ 5.4**

1. ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በየግላችሁ የምትወዱትን የእንግሊዝኛ ፊደል ጽፉችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

2. ተማሪዎች ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ በየግላችሁ የምትወዱትን የእንግሊዝኛ ፊደል ከጻፉችሁ በኂላ የምትወዱትን ቀለም ቀብታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ

### 5.3.6 ስነ-ጥበብ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን ለመማር ያለው ጠቀሜታ

እይታዊና ክዉናዊ ጥበባት የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር፣ የአመጋገብ ፣ የመረዳዳት በአጠቃላይ የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ልማድ እና እሴት በስዕል ፣በሙዚቃና በቴያትር ለልጆች ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሀገራችንን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የህዝብ አሰፋፈርእንዲሁም ማህበረሰቡ በእለት ከእለት ኑሮው ዉስጥ ስለሚያከናዉናቸው ተግባራት በእይታዊና ክዉን ጥበባት አማካኝነት ማስተማር ይቻላል፡፡



ምስል 5.10፡ አብሮ መመገብ  የሚያሳይ ሰዕል

**የምዕራፉ ማጠቃለያ**

- የሰው አካል የየሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡ማለትም የሰውነት አካላችን በማወዛወዝ አስደናቂ የቡድን ሙዚቃን ለመፍጠር ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሙዝቀኛ የሚይዘውን የሙዚቃ መሣሪያ በሰውነት አካላችን መያዛችን በማይታመን ሁኔታ ተደራሽ ነው፡፡
- ሙዚቃ እና የእይታ ጥበብ እርስበርሰ የተሳሰሩ እና ተምሳሌታዊ ናቸው፡፡ አንደ ኪነ ጥበብ ቅርፅ እንከን የለሽ ወደ ሌለ ይለወጣል ሙዚቃ ከጥንት ጀምሮ ለብዙ እና የእይታ አርቲስቶች ማነቃቂያ እና መነሻ ነው፡፡

**ማጠቃለያ መልመጃ**

1. ስለምትወዱት የትምህርት አይነት አንድ የሙዚቃ ግጥም ጻፉ፡፡ለምሳሌ ስለ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ እንግሊዘኛ ወይም አማረኛ የሚገለጽ መዝሙር ግጥም ጻፉ፡፡
2. የግብይት ስርአት የሚያሳይ ስዕል ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
3. ትወና ትምህርትን ለመማር ያላቸው አስተዋጽኦ የሚያሳይ ድራማ ሰርታችሁ ለክፍል አሳዩ፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክልለኛዉን መልስ ምረጡ

1. ዜማ፣ስልተምት (ሪትም) ፣ሃርመኒ(ህብረ ዜማ)ያለቸዉ ድምፆች ሁሉ ____________ለማለት እንችላለን

   ሀ. ሙዚቃ ለ. ስዕል ሐ. ድራማ
2. የሙዚቃ አላባዊያን የሆነዉ የቱ ነዉ

   ሀ. ዜማ ለ. ሜሎዲ ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ
3. የእይታ ጥበብ አላባዊያን እና መህር የሆነ የቱ ነዉ

   ሀ. እንቅስቃሴ ለ. ስልተ ምት ሐ. ሪትም
4. ልጆች ቤት ዉስጥ ያዩትን የእናት የአባትን ባህሪ እና ድርጊት በምን ያሳያሉ

   ሀ. በጫዋታ(በትወና) ለ. በመረመድ ሐ. ሀ እና ለ መልስ ናቸዉ